ቅጽ 87 ቁጥር 857 መጋቢት 2005

# ዓለም አቀፍ የቀይ መስቀል ግምገማ



# የልማዳዊ ህግ

ICRC

**ዓለም አቀፍ**
**የቀይ መስቀል**
**ግምገማ**

## ዓላማና አድማስ

**ዓለም አቀፍ የቀይ መስቀል ግምገማ በዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ በየወቅቱ የሚዘጋጅ መጽሔት ነው:: ዓላማውም የሰብዓዊ መብት ጥበቃ ሕግጋትንና ፖሊሲዎችን እንዲሁም በጦርነት ጊዜና በትጥቅ ትግል ጊዜ የሚከሰቱ ችግሮችን ለመፍታት መወሰድ ስለሚገባቸው እርምጃዎች ማስተዋወቅ ነው:: ይህ መጽሔት ለየት ባለ መልኩ በሰብዓዊ መብት ህግጋት ዙሪያ ጠቃሚ ዕውቀትን ለማስጨበጥ ህግጋቱን ለማዳበር እና መሰረታዊ የሆኑ ሰብዓዊ መብቶች እንዳይጣሱ ለመከላከል አስተዋጽኦ ያደርጋል:: ይህ የግምገማ መጽሔት ወቅታዊ በሆኑ ሰብዓዊ መብቶች መጣስ ዙሪያ የውይይት መድረኮችን ስለሚከፍት የግጭቶችን መንስኤና በሰዎች ላይ የሚያስከትሉትን ችግር በጥልቀት ለመመርመር እድል ይሰጣል:: በመጨረሻም ይህ መጽሔት ስለዓለም አቀፍ ቀይ መስቀልና ቀይ ጨረቃ እንቅስቃሴ በተለይ ደግሞ ስለ አለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ ፖሊሲዎችና ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች ለአንባቢዎቹ ግንዛቤ ይሰጣል::**

## የዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ

**የዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ ከማንኛውም ወገንተኛነት ነፃ የሆነ ድርጅት ሲሆን ብቸኛ የሆነ ሰብዓዊ የጦርነትና የውስጥ ብጥብጥ ጉዳተኛ ለሆኑ ሰዎች ድጋፍ በመስጠት አካላቸውና ክብረ ህሊናቸው እንዳይጎዳ መንከባከብ ነው:: በብጥብጥ ጊዜ የሚሰጡ ዓለም አቀፍ እርዳታዎች ለተጎጂዎች በአግባቡ እንዲደርሱ ያስተባብራል ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ህግጋትና መመሪያዎች በተግባር እንዲውሉና የተጎጂዎች ስቃይ እንዲቀንስ ለማድረግ ጥረት ያደርጋል:: እ.ኤ.አ. በ1863 የተመሰረተው የዓለም አቀፍ ቀይመስቀልና የቀይ ጨረቃ እንቅስቃሴዎች ምንጭ ነው::**

## የኮሚቴው አባላት

ፕሬዚዳንት - ጃኮብ ኬለንበርግ

ምክትል ፕሬዚዳንት - አኔ ፔቲትፒየር

ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዚዳንት -ዣክ ፎርሰትር

| | |
|---|---|
| ጄን አብት | ክሎድ ልኮልቴር |
| ጄን ፊሊፕ አሳል | ዣክ ሞሪሎን |
| ክርስቲያን ቢርሊ | ጋብሪየሌ ናንቸን |
| ፓውሎ ቤርናስኮኒ | የቭስ ሳንዶዝ |
| ኧርነስት ኤ. ብሩገር | ዳንኤል ቱረር |
| ሳሲ ብሩሽዌይለር | ኦሊቪየር ቮዶዝ |
| ጄን ድ ኮርቴን | አንድሬ ቮን ሞስ |
| ፓውላ ጂላኒ | |

## ዋና አዘጋጅ

ቶኒ ፋነር
*ዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ*

## የአዘጋጆች ቦርድ

አህመድ አቡ ኤል ዋፋ
*ካይሮ ዩኒቨርሲቲ፣ ግብጽ*

ዳንኤል ባር ታል
ቴልአቪቭ ዩኒቨርሲቲ፣ እስራኤል

አኔት ቤከር
ፓሪስ ዩኒቨርሲቲ፣ ፈረንሳይ

አንቶኒዎ ካንካዶ ትሪንዳዴ
ብራዚሊያ ዩኒቨርሲቲ፣ ብራዚል

ማሪካ ፋህሌን
የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ስቶኮልም፣ ስዊድን

ቤርናርድ ሀይኬል
ኒው ዮርክ ዩኒቨርሲቲ ዩ. ኤስ አሜሪካ

ቪ ኤስ ማኒ
ጉጅራት የህግ ዩኒቨርሲቲ፣ ጋንዲንጋር፣ ጉጅራት፣ ህንድ

ሔርፈሬድ ሙንክለር
ሀምቦልድ ዩኒቨርሲቲ፣ በርሊን፣ ጀርመን

ሞና ሪሽማዊ
የተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን፣
ጄኔቭ

ኤልዛቤት ሳልሞን ጋራት
የፔሩ ፓንቲፊካ ካቶሊክ ዩኒቨርሲቲ፣ ሊማ፣ ፔሩ

ማርኮ ሳሶሊ
የጄኔቭ ዩኒቨርሲቲ፣ ስዊዘርላንድ

ሚካኤል ኤን ሽሚት
ጆርጅ ሲ ማርሻል የአውሮፓ የፀጥታ ጥናቶች ማዕከል፣
ጋርሚሽ፣ ፓርቴንክሪቴን፣ ጀርመን

ቴረንስ ቴለር
ዓለም አቀፍ የስትራቴጅ ጥናት ማዕበል፣ ለንደን፣
ዋሽንግተን ዲ.ሲ፣ ዩ፣ኬ/ዩ.ኤስ. ኤ.

ባኪትያር አር ቱዝሙካሜዶቭ
ዲፕሎማቲክ አካዳሚ፣ መስኮብ፣ የሩሲያ
ፌዴሬሽን

ዌን ኮ ዙ
የህግ ትምህርት ቤት፣ የቻይና ሬንማን
ዩኒቨርሲቲ፣ ቤጅንግ፣ የህዝባዊት ቻይና ሪፑብሊክ

# የልማዳዊ ህግ

## በልማዳዊ አለም አቀፍ የሠብአዊነት ህግ ላይ የተደረገ ጥናት፡ (በትጥቅ ግጭት ወቅት ያለው ህግ እንዲታወቅና እንዲከበር አስተዋፅኦ ለማድረግ የቀረበ)

**ዣን - ሜሪ ሄንኬርትስ***

*ዣን - ሜሪ ሄንኬርትስ የዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ የህግ መምሪያ የህግ አማካሪና የዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ የልማዳዊ አለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግ ኘሮጀክት መሪ ናቸው፡፡ በቅርቡም ከሉዊስ ዶስዋልድ - ቤክ ጋር በልማዳዊ አለም አቀፍ የሠብአዊነት ህግ ላይ የተፃፈ አንድ ባለ ሁለት ቅፅ ሥራ አርታኢ ሆኖ ያዘጋጀ ሲሆን ስራውም በኬምብሪጅ ዩኒቨርስቲ ኘሬስ ታትሟል፡፡*

### ጭምቅ ሀሳብ

*ይህ መጣጥፍ በቀይ መስቀል እና ቀይ ጨረቃ አለም አቀፍ ጉባኤ ጥያቄ መሠረት በልማዳዊ አለም አቀፍ የሠብአዊነት ህግ ላይ በቅርቡ በዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ ከተካሄደ ጥናት ጀርባ ያለውን ምክንያት ያብራራል፡፡ መጣጥፉ ጥናቱ የተከተለውን ዘዴ እና እንዴት እንደተደራጀ የሚያቀርብ ሲሆን አንዳንድ ዋና ዋና ግኝቶችንም አጠቃልሎ*

* የዚህ ፅሁፍ ደራሲ ፅሁፉን በሚያዘጋጅበት ወቅት እርዳታ ላደረጉለትና አስተያየት ለሰጡት ለኤሪክ ሞንጌል፣ ሉዊስ ዶስዋልድቤክ እና ለህግ መምሪያ ባልደረቦች በሙሉ ምስጋናውን ያቀርባል፡፡ በዚህ ፅሁፍ ውስጥ የሰፈሩት ሀሳቦች በሙሉ የደራሲው እንጂ የዓለም አቀፍ ቀይ መስቀልን አቋም አያንፀባርቁም፡፡

*ያቀርባል፡፡ ይሁን እንጂ የእነዚህ ግኝቶችን የተሟላ ቅኝትና ትንተና ያቀርባል ማለት አይደለም፡፡*

: : : : : : : : : : : : : : : : : : : : : : : : : :

## *መግቢያ*

የ1949ኙ የጄኔቫ ስምምነቶች ከፀደቁበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት 50 አካባቢ አመታት የሠው ልጅ ሁሉንም አህጉሮች ያዳረሱ ቁጥራቸው በአስደንጋጭ ሁኔታ የበዛ የጦር ግጭቶች አጋጥመውታል፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ የ1977ቱ አራቱ የጄኔቫ ስምምነቶችና ተጨማሪ ኘሮቶኮሎቻቸው በግጭቶች ውስጥ ለማይሳተፉ ወይም መሣተፋቸውን ላቆሙ (የቆሠሉ፣ የታመሙ፣ እና በባህር ላይ አደጋ ለደረሰባቸው፣ ከጦር ግጭት ጋር በተያያዘ ምክንያት ነፃነታቸውን የተነፈጉ፣ እና ሲቪሎች) ሰዎች ህጋዊ ጥበቃ አድርገዋል፡፡ ቢሆንም ግን በርካታ የእነዚህ ስምምነቶች ጥሰቶች የተከሰቱ ሲሆን በጥሰቱም ምክንያት አለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግ በተሻለ ሁኔታ ተከብሮ ቢሆን ኖሮ ሊወገዱ ይችሉ የነበሩ ስቃይ እና የህይወት መጥፋት ተከስተዋል፡፡

ይህን በተመለከተ ያለው አጠቃላይ አስተያየት አለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግ ጥሰቶች የሚከሰቱት ደምቦቹ ብቃት ስለሌላቸው አይደለም፡፡ ጥሰቶቹ የሚከሰቱት ደምቦቹን ለማክበር ካለ የፍላጎት ማነስ፣ ደምቦቹን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ነገሮች በብቃት አለመገኘት በአንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ የደምቦቹን አፈፃፀም በተመለከተ የሚኖር እርግጠኛ አለመሆን፣ እና በፖለቲካ መሪዎች፣ በአዛዦች፣ በተዋጊዎችና በአጠቃላይ በህዝቡ አካባቢ ያለ የግንዛቤ እጥረት ምክንያት ነው፡፡

እ.ኤ.አ. ከኦገስት እስከ ሴኘቴምበር 1993 ዓ.ም በጄኔቫ ተካሂዶ የነበረው የጦርነት ተጠቂዎችን የመከላከል አለም አቀፍ ጉባኤ በተለይ የአለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግ ጥሰቶችን የማስተናገጃ መንገዶችን የተወያየባቸው ቢሆንም አዲስ የስምምነት

ድንጋጌዎች እንዲፀድቁ ያቀረበው ጥቆማ አልነበረም፡፡ በምትኩ ጉባኤው በሙሉ ስምምነት ባፀደቀው የመጨረሻ መግለጫው "የሠብአዊነት ህግ አፈፃፀምን የበለጠ ውጤታማ ማድረግ ያለውን አስፈላጊነት" በድጋሚ በአፅንኦት በመግለፅ የስዊስ መንግስት "ህጉን በተሟላ ሁኔታ ለማስከበር የሚያስችሉ ተግባራዊ መንገዶችን የሚያጠና አንድ ከመንግስታት የተውጣጣ የኤክስፐርቶች ቡድን እንዲያቋቁምና ሪፖርቱን ለሚቀጥለው የቀይ መስቀልና ቀይጨረቃ አለም አቀፍ ጉባኤ ላይ እንዲቀርብ እንዲያዘጋጅ"[1] ጥሪ አቅርቦለታል፡፡

የጦርነት ተጠቂዎችን ለመጠበቅ ከመንግስታት ተወጣጥቶ የተቋቋመው የኤክስፐርቶች ቡድን እ.ኤ.አ በጃንዋሪ 1995 ዓ.ም. ጄኔቫ ውስጥ ተሰብስቦ አለም አቀፍ የሠብአዊነት ህግ እንዲከበር በተለይ ህጉን በተመለከተ የተሻለ እውቀትና የተሻለ የአፈፃፀም ብቃት ሊያመጡ የሚችሉ የመከላከል ዘዴዎች ላይ ያነጣጠሩ በርካታ የመፍትሄ ሃሣቦችን አፅድቋል፡፡ ከመንግስታት ተውጣጥቶ የተቋቋመው የኤክስፐርቶች ቡድን ያፀደቀው የመፍትሄ ሃሣብ የሚጠይቀው *የዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ* የተለያዩ ጂኦግራፊያዊ ክልሎችን እና የተለያዩ የህግ ስርአቶችን በሚወክሉ የአለምአቀፍ የሠብአዊነት ህግ ኤክስፐርቶች ድጋፍ እንዲሁም ከመንግስታትና አለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር በመመካከር በአለም አቀፍ እና አለም አቀፍ ባልሆኑ ግጭቶች ውስጥ ተፈፃሚ የሚሆን የአለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግ ደምቦችን የያዙ ሪፖርት አዘጋጅቶ ሪፖርቱን ለሀገሮችና ብቃት ላላቸው አለም አቀፍ አካላት እንዲያሠራጭ ነው፡፡[2]

የሰብአዊነት ደንቦችን የያዙ ሪፖርት አዘጋጅቶ ሪፖርቱን ለሀገሮችና ብቃት ላላቸው አለም አቀፍ አካላት እንዲያሰራጭ ነው፡፡ እ.ኤ.አ. በዲሴምበር 1995 ዓ.ም 26ኛው

---

[1] International Conference for the Protection of War Victims, Geneva 30 August – September 1993, Final Declaration, International Review of the Red Cross, No. 296,1993, p.381

[2] Meeting of the Intergovernmental Group of Experts for the Protection of War Victims, Geneva, 23-27 January 1995 Recommendation II, International Review of the Red cross. No. 310,1996., p.84.

የቀይ መስቀልና የቀይ ጨረቃ አለም አቀፍ ጉባኤ ይህንን ጥያቄ ተቀብሎ በማፅደቅ *የዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ* ዓለም አቀፍ ባልሆኑ የጦር ግጭቶች ውስጥ ተፈጻሚነት ያለው ሪፖርት እንዲያዘጋጅ ኦፊሴላዊ ህጋዊ ስልጣን ሠጥቶታል፡፡[3] ከአስር አመት አካባቢ በኂላ ማለትም እ.ኤ.አ. በ2005 ዓ.ም ከሠፊ ምርምርና ከኤክስፐርቶች ጋር ከተደረገ ሠፊ ምክክር በኂላ አሁን ልማዳዊ አለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግ ጥናት እየተባለ የሚጠራው ይህ ሪፖርት ታትሟል፡፡[4]

## ዓላማ

በልማዳዊ ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግ ላይ የተደረገው ጥናት ዓላማ በዓለም አቀፍ የሠብአዊነት የውል ህግ አተገባበር ጋር የተገናኙ አንዳንድ ችግሮችን ለማስወገድ ነበር፡፡ የስምምነት ህግ በደምብ የተዘጋጀ ሲሆን የተፈቀዱ ለበርካታ ሰዎች ጥበቃ የሚያደርግና ጦርነት የማካሄጃ መንገዶችና ዘዴዎችን የሚወስን በርካታ ጦርነት ነክ ጉዳዮችን የሚሸፍን ህግ ነው፡፡ የጄኔቫ ስምምነቶችና ተጨማሪ ኘሮቶኮሎቻቸው በግጭቶች ውስጥ በቀጥታ ተሳታፊ ላልሆኑ ወይም ተሳታፊነታቸውን ላቆሙ ሰዎች ጥበቃ የሚያደርጉ በርካታ ድንጋጌዎችን ይዘዋል፡፡ በስምምነት ህግ ውስጥ ያለው የጦርነት ማካሄጃ መንገዶችና ዘዴዎች ደምብ የጀመረው እ.ኤ.አ. በ1868 የቅዱስ ፒተርስበርግ አዋጅ፣ የ1899 እና የ1907 የሔግ ደምቦች እና የ1925 የጄኔቫ የጋዝ ኘሮቶኮል፣ ሲሆን በቅርቡም የ1972 የባዮሎጂካዊ የጦር መሣሪያዎች ስምምነት፣ የ1977 ተጨማሪ ኘሮቶኮሎች፣ የ1980 የተወሰኑ የተለምዶ የጦር መሣሪያዎች ስምምነትና አምስቱ ኘሮቶኮሎቹ፣ የ1993 የኬሚካላዊ የጦር መሣሪያዎች ስምምነትና፣ የ1997

---

[3] 26th International conference of the Red cross and Red Crescent, Geneva, 3-7 December 1995, Reference of the Red cross and Red Crescent, Geneva, 3-7 December 1995, Resolution 1, International Humanitarian Law: From Law to Action : Report on the follow-up to the International conference for the Protection of War Victims, International Review of the Red Cross No. 310,1996, p.58

[4] Jean-Marie Henckaerts and Louise Doswald – Beek, Curstomary International Humanitarian Law, 2 volumes, volume 1 Rules, Volume II Practice (2 parts), Cambridge University Press, 2005

የኦታዋ የፀረ-ሠው ፈንጂዎች ክልከላ ስምምነት ውስጥም ተካትቷል፡፡ በጦር ግጭቶች ውስጥ መኖር የሚገባው የባህላዊ ንብረት ጥበቃ በ1954 የሔግ ስምምነትና ሁለቱ ኘሮቶኮሎቹ ውስጥ ዝርዝር ሥርዐት ወጥቶለታል፡፡ የ1998 የአለም አቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤት ደምብ ካካተታቸው ውስጥ ፍርድ ቤቱ ባለው የህግ ስልጣን የሚመለከታቸው የጦር ወንጀሎች ዝርዝር ይገኝበታል፡፡

ይሁን እንጂ በአሁኑ ወቅት በልማዳዊ ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግ ላይ የሚደረግን ጥናት አስፈላጊና ጠቃሚ የሚያደርጉት በአሁኑ ወቅት ባሉ የጦር ግጭቶች ወቅት በእነዚህ ስምምነቶች አፈፃፀም ላይ ያሉ ሁለት እንቅፋቶች ናቸው፡፡ በመጀመሪያ ስምምነቶች የሚሠሩት በፈራሚ ሀገሮች ውስጥ ብቻ ነው፡፡ ይህም በተለያዩ የጦር ግጭቶች ውስጥ በግጭቶቹ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑት ሀገሮች በፈረሟቸው ስምምነቶች መሠረት የተለያዩ የአለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግ ስምምነቶች ተፈፃሚ ይሆናሉ ማለት ነው፡፡ አራቱ የ1949 የጄኔቫ ስምምነቶች በመላው አለም የፀደቁ ቢሆንም ሁሉም ሠነዶች ለምሣሌ ተጨማሪ ኘሮቶኮሎቹ በዚህ መልኩ አልፀደቁም፡፡ ምንም እንኳን ተጨማሪ ኘሮቶኮል I ከ160 በላይ በሆኑ ሀገሮች የፀደቀ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት በአለም አቀፍ የጦር ግጭቶች ውስጥ ተሣታፊ የሆኑ በርካታ ሀገሮች ፈራሚ ባለመሆናቸው መፍትሄነቱ የተገደበ ነው፡፡ በተመሣሣይም ምንም እንኳ 160 የሚጠጉ ሀገሮች ተጨማሪ ኘሮቶኮል II ን ያፀደቁ ቢሆንም አለም አቀፍ ያልሆኑ የጦር ግጭቶች እየተካሄዱባቸው ያሉ በርካታ ሀገሮች ኘሮቶኮሉን ያፀደቁ አይደሉም፡፡ በእነዚህ አለም አቀፍ ባልሆኑ የጦር ግጭቶች ውስጥ ብዙውን ጊዜ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችለው ብቸኛው ድንጋጌ የጄኔቫ ስምምነቶች የጋራ የሆነው አንቀፅ 3 ብቻ ነው፡፡ ስለዚህም የጥናቱ የመጀመሪያ ዓላማ የነበረው በግጭት ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ወገኖች በሙሉ ተመሣሣይ ደምቦችን የያዙ ስምምነቶችን ቢያፀድቁም ባያፀድቁም የትኞቹ የአለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ደምቦች የልማዳዊ አለም አቀፍ ህግ አካላት እንደሆኑና ስለዚህም በሁሉም በግጭት ውስጥ ተሳታፊ በሆኑ

ወገኖች ላይ ተፈፃሚ እንደሆኑ ማወቅ ነበር፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የሰብአዊነት የስምምነት ህግ በአሁኑ ወቅት ያሉትን አብዛኛዎቹን አለም አቀፍ ያልሆኑ የጦር ግጭቶች በበቂ ዝርዝር ስርዐት አላበጀላቸውም፡፡ ለዚህም ምክንያቱ እነዚህ ግጭቶች አለም አቀፍ ከሆኑ የጦር ግጭቶች ጋር ሲነፃፀሩ በቁጥር አነስተኛ ለሆኑ የስምምነት ደንቦች ተገዥ በመሆናቸው ነው፡፡ አለም አቀፍ ባልሆኑ የጦር ግጭቶች ወቅት ተፈፃሚነት ያላቸው የተወሰነ ቁጥር ያላቸው ስምምነቶች ብቻ ናቸው፡፡ እነርሱም፡- የተሻሻለው የተወሰኑ የጦር መሣሪያዎች ስምምነት፣ የዓለም አቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤት ህግ፣ የኦታዋው የፀረ ሠው ፈንጂዎች ክልከላ ስምምነት፣ የኬሚካላዊ የጦር መሣሪያ ስምምነት፣ የሄግ የባህላዊ ንብረት ጥበቃ ስምምነትና ሁለተኛው ኘሮቶኮሉ፣ እንዲሁም ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የጄኔቫ ስምምነቶች ተጨማሪ ኘሮቶኮል II እና የስምምነቶች የጋራ የሆነው አንቀፅ 3 ናቸው፡፡ ምንም እንኳን የጋራ አንቀፅ 3 መሠረታዊ ጠቀሜታ ያለው ቢሆንም የሚያቀርበው መጠነኛ የሆነ መሟላት ያለባቸውን ደረጃዎች ማዕቀፍ ብቻ ነው፡፡ ተጨማሪ ኘሮቶኮል II በሚጠቅም ሁኔታ የጋራ አንቀፅ 3ን የሚያግዝ ቢሆንም እርሱም ቢሆን አለም አቀፍ የሆኑ የጦር ግጭቶችን ከሚመለከቱት የጄኔቫ ስምምነቶችና ከተጨማሪ ኘሮቶኮል I ያነሱ ዝርዝሮችን የያዘ ነው፡፡

ተጨማሪ ኘሮቶኮል II 15 አንቀጾችን የያዘ ሲሆን ተጨማሪ ኘሮቶኮል I ግን ከ80 በላይ አንቀጾችን ይዟል፡፡ ምንም እንኳን ቁጥሮችን ብቻ በመመልከት ሁሉንም ነገር ማወቅ የማይቻል ቢሆንም እነዚህ ቁጥሮች የስምምነት ህግ አለም አቀፍ በሆኑና ባልሆኑ የጦር ግጭቶች መካከል በተለይ ዝርዝር ደምቦችና ብይኖችን (definitions) በተመለከተ ያለው ከፍተኛ ልዩነት ያሳያሉ፡፡ ስለዚህም የጥናቱ ሁለተኛ አላማ ልማዳዊ ዓለም አቀፍ ህግ ዓለም አቀፋዊ ላልሆኑ የጦር ግጭቶች ስርአት ያበጅ እንደሆነና የሚያበጅ ከሆነም እስከ ምን ድረስ እንደሆነ ለማወቅ ነበር፡፡

**ጥናቱ የተከተለው ዘዴ (methodology)**

የዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ህግ ልማዳዊ አለም አቀፍ ህግን "እንደህግ ሆኖ ተቀባይነት ያገኘ አጠቃላይ አሠራር"[5] ነው በማለት ይገልፀዋል፡፡ በስፋት እንደሚታመነው የልማዳዊ አለም አቀፍ ህግ ደምብ መኖር የሁለት ነገሮች መኖርን ይጠይቃል፡፡ እነርሱም ሀገራዊ አሠራር (USUS) እና እንደደንቡ ባህርይ እንደ ህግ የተከለከለ ወይም የተፈቀደ እንዲህ አይነት አሠራር መኖር አለበት የሚል እምነት (Opinion jurissive necessitates) ናቸው፡፡ አለም አቀፉ ፍርድ ቤት በ 'continental shelf case' ውስጥ እንዳስቀመጠው "በእርግጥ የልማዳዊው አለም አቀፍ የተመሰረተበት ህግ ማቴሪያል መታየት የሚያስፈልገው በመጀመሪያ በሀገሮቹ አሠራርና የሕግ እምነት (opinio juris) ውስጥ መሆኑ እውነት ነው"፡፡[6] የእነዚህ የሁለቱ ትክክለኛው ትርጉምና ይዘት የበርካታ ትምህርት ነክ ፅሁፎች ርዕስ ሆነዋል፡፡ ጥናቱ አጠቃላይ የልማዳዊ አለም አቀፋዊ ህግ ደምብ መኖሩን ለማወቅ የተከተለው መንገድ የቆየና በአለም አቀፉ ፍርድ ቤት በተለይ በ "North Sea Continental Shelf case"[7] ውስጥ የተቀመጠው ነበር፡፡

## ሀገራዊ አሠራር

ሀገራዊ አሰራር ከሁለት አቅጫዎች መታየት አለበት፡፡ የመጀመሪያው ለልማዳዊ አለም አቀፍ ህግ መፈጠር አስተዋፅኦ የሚያደርገው ምንድን ነው (የሀገራዊ አሠራር ምርጫ) ለሚለው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ይህ አሠራር ልማዳዊ አለም አቀፍ ህግ ደምብን ይመሠርታል ወይ (የሀገራዊ አሠራር ግምገማ) የሚለው ነው፡፡

---

5 Statute of the International Court of Justice, Article 38(1) (b)

6 International Court of Justice, continental Shelf case (Libyan Arab Jama hiriya V.Marta), Judgment 3 June 1985, ICJ Reports 1985, pp.29-30 & 27

7 International Court of Justice, North Sea Continental Shelf Cases, Judgment, 20 February 1969 ICJ Reports 1969,p.3

### *የሀገራዊ አሰራር ምርጫ*

የሀገሮች አካላዊም ሆነ ቃላዊ ድርጊቶች ልማዳዊ አለም አቀፍ ህግ እንዲፈጠር አስተዋፅኦ የሚያደርገው አሠራር አካላት ናቸው፡፡ አካላዊ ድርጊት ከሚያካትታቸው መካከል ለምሣሌ የውጊያ ሜዳ ባህርይ ማለትም የተወሠኑ የጦር መሣሪያዎች አጠቃቀምና ለተለያዩ አይነት ሰዎች የሚደረግ አያያዝን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ቃላዊ ድርጊቶች ደግሞ ወታደራዊ መመሪያዎችን፣ ብሔራዊ ህጎችን፣ ብሔራዊ case-law ፣ ለጦርና ለደህንነት ሀይላት የሚሠጡ ትዕዛዞችን፣ በጦርነት ወቅት ያሉ ወታደራዊ ግንኙነቶችን፣ ዲኘሎማሲያዊ ተቃውሞዎችን፣ የኦፊሴላዊ የህግ አማካሪዎች አስተያየቶችን፣ በስምምነት ረቂቆች ላይ በመንግስታት የሚሠጡ አስተያየቶችን፣ የስራ አስፈፃሚ (executive) ውሳኔዎችና ደምቦችን፣ በአለም አቀፍ ችሎቶች ፊት የሚቀርቡ ይግባኞችን፣ በአለም አቀፍ መድረኮች ላይ የሚሠጡ መግለጫዎችን፣ ያጠቃልላሉ፡፡ ይህ ዝርዝር የሚያሳየው የአንድ ሀገር ህግ አስፈፃሚ ህግ አውጪና የዳኝነት አካላት አሠራሮች ልማዳዊ አለም አቀፍ ህግ እንዲመሠረት አስተዋፅአ እንደሚያደርጉ ነው፡፡

በአለም አቀፍ ድርጅቶች ወይም ጉባኤዎች በውሳኔዎች ላይ የሚደረጉ የድርድርና የማፅደቅ ስራዎች ስለ ድምፅ አሠጣጥ ከሚሠጡ ማብራሪያዎች ጋር ተዳምረው ተሳታፊ የሆኑ ሀገሮች ድርጊቶች ናቸው፡፡ ከጥቂቶች በስተቀር ውሳኔዎች በተለምዶ አሣሪነት እንደሌላቸው ይታወቃል፡፡ ስለዚህም በልማዳዊ አለም አቀፍ ህግ ደምብ ምስረታ ግምገማን በተመለከተ ለማንኛውም ውሣኔ የሚሠጠው ዋጋ የሚወሰነው በይዘቱ ማለትም ባለው የተቀባይነት ደረጃና ግንኙት ካለው ሀገራዊ

አሠራር ጋር ባለው መጣጣም ነው፡፡[8] ለውሳኔው ያለው ድጋፍ ከፍ ካለ የሚሠጠው ጠቀሜታም እንዲሁም ከፍ ይላል፡፡

ምንም እንኳን የአለም አቀፍ ፍርድ ቤቶች ውሳኔዎች አለም አቀፍ ህግን በተመለከተ ደጋፊ ምንጮች ቢሆኑም[9] ሀገራዊ አሠራር አይደሉም፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤቶች እንደ ብሔራዊ ፍርድ ቤቶች የሀገር ልሣኖች ስላልሆኑ ነው፡፡ ቢሆንም ግን በአለም አቀፍ ፍርድ ቤቶች የሚሠጡ ውሣኔዎች ጠቃሚነት አላቸው፡፡ ምክንያቱም የአንድ አለም አቀፍ ፍርድ ቤት ልማዳዊ አለም አቀፍ ህግ መኖሩን የሚያሣይ ግኝት ይህንኑ በተመለከተ አሣማኝ መረጃ ስለሚሆን ነው፡፡ በተጨማሪም ውሳኔዎቻቸው በሚኖራቸው የቀዳሚነት (precedence) ዋጋ ምክንያት አለም አቀፍ ፍርድ ቤቶች በኋላ በሚኖሩ የሀገራት እና የአለም አቀፍ ድርጅቶች አሠራሮች ላይ ተፅዕኖ በማሣረፍ ለልማዳዊ አለም አቀፍ ህግ ደምብ መፈጠር አስተዋፅኦ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

እንደየስነስርዐት ደምብ፣ የተወሰኑ አለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግ ደምቦችን ለማክበር የሚገቡ ቃሎች እና ሌሎች መግለጫዎችን የመሣሠሉት ሀገራዊ አሠራር አይደሉም፡፡ እንዲህ አይነት አሠራር አለምአቀፍ ባልሆኑ የጦር ግጭቶች ውስጥ የተወሰኑ ደምቦች ተቀባይነት እንዳላቸው በመረጃነት የሚያሣይ ቢሆንም ያለው ህጋዊ ጠቀሜታ ግልፅ አይደለም፡፡ ስለዚህም ልማዳዊ አለምአቀፍ ህግ መኖሩን ለማረጋገጥ ይረዳል በሚል ትኩረት አልተደረገበትም፡፡ የዚህ አይነት አሠራር ምሣሌዎች በጥናቱ ቅፅ II ውስጥ “ሌሎች አሠራሮች” በሚል ርዕስ ስር ተዘርዝረዋል፡፡

---

[8] እነዚህ ሁኔታዎች ያላቸው ጠቀሜታ በአለም አቀፍ ፍርድ ቤት አፅንኦት ተሰጥቶት ቀርቧል፡፡ Legality of the Threat or use of Nuclear Weapons, Advisory Opinion, 8 July 1996, ICJ Reports 1996,pp.234,255 & 70-53.

[9] Statute of the International Court of Justice, Article 38(1) (d)

*የሀገራዊ አሠራር ግምገማ*

ሀገራዊ አሠራር ልማዳዊ አለም አቀፍ ህግ ለመፍጠር በሚያስችል በቂ ሁኔታ የመረጃ ክምችት (dense) እንዳለው ለማረጋገጥ መመዘን አለበት፡፡[10] የልማዳዊ አለምአቀፍ ህግ ደምብን ለመመስረት ሀገራዊ አሠራር ሙሉ በሙሉ አንድ አይነት፣ ስፋት ያለውና ወኪል ሊሆን ይገባል፡፡[11] ይህ ምን ማለት እንደሆነ ጠለቅ ብለን እንመልከት፡፡

በመጀመሪያ የልማዳዊ አለም አቀፍ ህግ ደምብ ለመመስረት ሀገራዊ አሠራር ሙሉ በሙሉ አንድ አይነት መሆን አለበት፡፡ የተለያዩ ሀገሮች በወሣኝ መልኩ በተለያዩ ሁኔታዎች የሠሩ መሆን የለባቸውም፡፡ የአለም አቀፍ ፍርድ ቤት የህግ ፍልስፍና እንደሚያሳየው በመጀመሪያ ሲታይ የአንድን አሠራር ወጥነት የሚፃረር የሚመስል አሠራር ይህ ተፃራሪ አሰራር በሌሎች ሀገሮች እስከተወገዘ ወይም በመንግስት በራሱ እስከተካሄደ ድረስ የልማዳዊ አለም አቀፍ ህግ ደምብ ምስረታን አያግድም፡፡ በእንደዚህ አይነት ውግዘት ወይም ክህደት አማካኝነት የተጠቀሠው ደምብ ማረጋገጫ ያገኛል፡፡[12]

ይህ አንድን ደምብ የሚደግፍ ሀገራዊ አሠራር እንዳለ የሚያሣይ በርካታ መረጃ እንዲሁም ያ ደምብ ለመጣሱ ተደጋጋሚ መረጃ ጋር ተዳምሮ ለበርካታ አለምአቀፍ የሰብአዊነት ህግ ደምቦች የተለየ ጠቀሜታ አለው፡፡

---

[10] "dense" የሚለው አገላለፅ በዚህ አገባቡ የወደው ከ ሰር ሐምፍሬ ዋልዶክ "General Course on Public International Law" Collected courses of the Hague Academy of International Law, vol.106,1962, ገፅ 44 ነው፡፡

[11] International Court of Justice, North Sea Continental Shelf cases, ጥቁም ስራ (note 7) ገጽ 43& 74

[12] International Court of Justice, Case Concerning Military and Paramilitary Activities in and against Nicaragua (Nicaragua Vs United States), Merits, Judgment, 27 June 1986, ICJ Reports 1986, p.98 & 186 ተመልከት

ጥሰቶችን በተመለከተ በሚመለከተው ወገን ይቅርታዎች ሲደረጉና ትክክለኛነታቸው ተቀባይነት ሲያገኝ እና/ወይም በሌሎች ሀገሮች ውግዘት ሲደርስባቸው እነዚህ የተጠቀሠው ደምብ መኖሩን ከጥያቄ ውስጥ የሚያስገቡ አይደሉም። ያለን ልማዳዊ የአለም አቀፍ ህግ ደምብ መለወጥ የሚፈልጉ ሀገሮች ይህንኑ በኦፊሴላዊ አሠራራቸው አማካኝነት ማድረግና መብታችንን ተጠቅመን ነው ያደረግነው ማለት ይችላሉ።

በሁለተኛ ደረጃ የአጠቃላይ ልማዳዊ አለምአቀፍ ህግ ደምብ እንዲፈጠር የሚመለከተው ሀገራዊ አሰራር ስፋት ያለውና ወኪል ሊሆን ይገባል። ይሁን እንጂ አለም አቀፍ መሆን አያስፈልገውም። "አጠቃላይ" አሠራር መሆኑ ይበቃል።[13] ምንም ቁርጥ ያለ የሀገሮች ቁጥር ወይም ፐርሰንቴጅ አያስፈልግም። ለዚህ አንዱ ምክንያት የሚፈለገው የተሳትፎ መጠንን በቁጥር መግለፅ ስለማይቻልና ይህ መስፈርት ጥያቄው ስንት ሀገሮች ተሳተፉ ብቻ ሣይሆን የትኞቹ ሀገሮች የሚልም ስለሆነ ነው።[14] አለም አቀፉ ፍርድ ቤት North Sea Continental shelf cases ውስጥ እንዳስቀመጠው አሠራሩ "ፍላጎታቸው በተለይ የሚነካባቸውን ሀገሮች መጨመር" አለበት።[15]

ይህ ምልከታ ሁለት አንደምታዎች አሉት፡ (1) ሁሉም "በተለይ የሚነኩ" ሀገሮች ከተሣተፉ አብዛኞዎቹ ሀገራት በንቃት መሣተፋቸው አስፈላጊ አይሆንም። ነገር ግን ቢያንስ "በተለይ የሚነኩ" ሀገሮች ካላቸው አሠራር ጋር የሚስማሙ ሊሆኑ ይገባል። (2) "በተለይ የሚነኩ ሀገሮች" አሠራሩ የማይቀበሉ ከሆነ እንደተገለፀው

---

[13] International Law association, final Report of the Committees on the formation of Customary (General) International Law, Statement of principles Applicable to the formation of General Customary International Law, Report of the Sixty-Ninth conference, London, 2000, Principle 14.p.734 ከዚህ በኋላ "ILA ሪፖርት ተብሎ የሚጠቀስ"

[14] ibid., commentary (d) and (e) to principle 14.pp.736-737.

[15] International Court of Justice, North Sea Continental shelf Cases, Opicit. (note 7), p.43. &74

አንድ አይነት መሆን የማያስፈልግ ቢሆንም ወደየልማዳዊ አለም አቀፍ ደምብነት ሊያድግ አይችልም፡፡[16] በአለም አቀፉ የሰብአዊነት ህግ መሠረት "በተለይ የሚነኩ" የሚለው እንደየሁኔታው ይለያያል፡፡ ለምሣሌ ዕይታን የሚከለክሉ የጨረር መሣሪያዎች አጠቃቀምን በተመለከተ "በተለይ የሚነኩ" የሚለው የሚያካትታቸው ምንም እንኳን ሌሎች ሀገሮች መሣሪያዎቹ በስራ ላይ ሲውሉ ሊጎዱ የሚችሉ ቢሆንም እንደዚህ አይነት መሣሪያዎችን በማምረት ሂደት ላይ እንደሆኑ የታወቁ ሀገሮችን ነው፡፡ በተመሣሣይም ህዝባቸው ሰብአዊ ዕርዳታ የሚያስፈልገው ሀገሮች እንደዚሁም በተደጋጋሚ ይህን ዕርዳታ የሚያቀርቡ ሀገሮች "በተለይ የሚነኩ" ናቸው፡፡ የትኛውንም አለም አቀፍ የሰብአዊነት ደምብ በተመለከተ በጦር ግጭት ውስጥ የተሣተፉ ሀገሮች የተወሰነ ደምብን በተመለከተ አሠራራቸው ሲገመገም ለዚያ የጦር ግጭት አግባብነት ካለው "በተለይ የሚነኩ" ናቸው፡፡ ምንም እንኳን በተወሰኑ አለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግ አካባቢዎች በተለይ የሚነኩ ሀገሮች ሊኖሩ ቢችሉም ሁሉም ሀገሮች በግጭቱ ተሳታፊ ባይሆኑም አለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግ በሌሎች ሀገሮች እንዲከበር የመጠየቅ ህጋዊ ፍላጎት እንዳላቸውም የማታወቅ ዕውነት ነው፡፡[17] በተጨማሪም ሁሉም አገሮች ሌሎች ሀገሮች ጦርነትን ለማካሄድ በሚጠቀሙባቸው መንገዶችና ዘዴዎች ምክንያት ተጎጂ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ስለዚህም "በተለይ የሚነኩ" የሚለው አገላለፅ በሚሠጠው ቀጥተኛ ትርጉም ቢካተቱም ባይካተቱም የሁሉም ሀገሮች አሠራር ከግምት ውስጥ መግባት አለበት፡፡

ጥናቱ ከአለም አቀፍ ሰብአዊነት ህግ ልማዳዊ ደምቦች ጋር በተያያዘ ቋሚ ተቃዋሚ (Persistent objector) ለመሆን በህግ ይቻል እንደሆነ ለማየት ምንም አስተያየት አልያዘም፡፡ በርካታ አስተያየት ሰጪዎች jus cogens ደምቦችን በተመለከተ ቋሚ ተቃዋሚ መሆን አይቻልም ብለው የሚያምኑ ቢሆንም ቋሚ

---

[16] ILA Report, opicit. (note 13), Commentary (e) to Principle 14,p.737

[17] . See Customary International Humanitarian Law, Opcit (note 4), Vol. I, Commentary to Rule 144

ተቃዋሚ የሚለው ፅንሠ ሀሣብ ያለውን ቀጣይ ተአማኒነት የሚጠራጠሩ ሌሎችም አሉ፡፡[18] ቋሚ ተቃዋሚ መሆን ከህግ አንፃር ይቻላል የሚለውን የሚቀበል ካለ፡ ጉዳዩ የሚመለከተው ሀገር ከመጀመሪያው አንስቶ አዲስ ልማድ መፈጠሩን የተቃወመና ተቃውሞውንም ያለማቋረጥ የቀጠለ መሆን አለበት፡፡ "ቋሚ ተቃዋሚ" መሆን አይቻልም፡፡[19]

አንድ የልማዳዊ አለም አቀፍ ህግ ደምብ እስከሚፈጠር ድረስ የተወሰነ ጊዜ የሚያልፍ ቢሆንም የተወሰነ የጊዜ ገደብ የለም፡፡ በምትኩ ወሣኝ ነጥብ የሚሆነው አሠራር በአንድ አይነት፣ በስፋትና ወኪል በሆነ መልኩ በበቂ ሁኔታ መከማቸቱ ነው፡፡[20]

## የህግ አስተያየት (Opinio juris)

የልማዳዊ አለምአቀፍ ህግ ደምብ መኖሩን ለማረጋገጥ የህግ አስተያየት ማስፈለጉ የሚያመለክተው አንድ አሠራር "እንደ መብት" መከናወኑን የሚያረጋጋጠውን የህግ እምነት ነው፡፡ አሠራሩና የህግ እምነቱ የሚገለፁበት መንገድ ደምቡ ክልከላ፣ ግዴታ ወይም የተወሰነ ባህሪይ የማሣየት መብትን ይዟል ወይስ አልያዘም በሚለው ላይ ተመርኩዞ ሊለያይ ይችላል፡፡

ጥናቱ እየተካሄደ በነበረበት ወቅት በአሠራር እና በህግ እምነት ውስጥ የሚካተቱትን ነጥቦች በትክክል የመለየቱ ስራ እጅግ አስቸጋሪና በአብዛኛው ንድፈ ሃሣባዊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ አብዛኛውን ግዜ የአንድ ድርጊት አሠራርም የህግ ዕምነትም ሆኖ ይገኛል፡፡ አለም አቀፉ የህግ ማህበር እንደጠቆመው አለምአቀፉ

---

18 ይህን ጉዳይ የመለከተ ዝርዝር ለማግኘት Maurice H. Mendelson, "The Formation of customary International Law", Collected Courses of the Hague Academy of International Law, vol.272, 1998 ገፅ 227-244ን ተመልከት፡፡

19 ILA Report, Opcit, (note 13), commentary (b) to Principle 15, p.738

20 Ibid., commentary (b) to Principle 12,p 731

ፍርድ ቤት "በበቂ ቃላት በልማዳዊ ህግ ውስጥ (አሉ ተብለው የሚታሰቡ) ግልፅ የሆኑ ነጥቦች ስላሉ ብቻ አንድ አሠራር ሁለቱንም ሊያሟይ አይችልም አላለም። በእርግጥ አብዛኛውን ግዜ ሁለቱን ነጥቦች መነጣጠል አስቸጋሪ ወይም እንደውም የማይቻል ነው።"[21] ይህ የሚሆንበት ምክንያት በተለይ እንደ ወታደራዊ መመሪያ ያሉ ቃላዊ ድርጊቶች ሀገራዊ አሠራር እንደሆኑ ስለሚቆጠርና ድርጊቶቹ በተጨማሪም የሀገሪቱን የህግ እምነት ስለሚያሟዩ ነው።

አሠራር በበቂ ክምችት ሲኖር በአጠቃላይ የህግ አስተያየት በዚያ አሠራር ውስጥ ይገኛል። ስለዚህም የህግ አስተያየት መኖሩን ነጥሎ ማሣየት ብዙውን ጊዜ አስፈላጊ አይደለም። አሠራሩ ግልፅ ባልሆነባቸው ሁኔታዎች ውስጥ ግን የህግ አስተያየት አሠራሩ ለልማድ መመስረት አስተዋፅኦ ያደርግ እንደሆነ ለመወሰን ጠቃሚ የሆነ ሚና ይጫወታል። ብዙውን ጊዜ ይህ ድርጊቶችን ካለመፈፀም ማለትም ሀገሮች ድርጊቶችን ሳይፈፅሙ ወይ ምላሽ ሳይሠጡ ሲቀሩና ምክንያቱ ግልፅ ሣይሆን ሲቀር የሚከሠት ነው። አለም አቀፉ ፍርድ ቤትም ሆነ ቀድሞት የነበረው የአለምአቀፍ ፍትህ ቋሚ ፍርድ ቤት ግልፅ ያልሆኑ አሠራሮች ልማዳዊ አለምአቀፍ ህግን ለመመስረት አስተዋፃኦ ያደርጉ እንደሆነ ለማወቅ የሚያስችል የተለየ የህግ አስተያየት መኖሩን ለማረጋገጥ የሞከሩት በእንደዚህ አይነት ሁኔታዎች ውስጥ ነበር።[22]

---

[21] Ibid., p.718 & 10(c). For an in-depth analysis of this question, see Peter Haggenmacher, "La doctrine des deux elements du droit coutumier dansla Pratique de la Cour international", Reveue générale de droit international public, vol.90,1986,p.s.

[22] See, e.g. Permanent court of International Justice, Lotus case (France V.Turkey), Judgement, 7 September 1927, PCIJ ser. A, No.10, p.28 (the Court found that States had not abstained from prosecuting wrongful acts abroad ships because they felt prohibited from doing so); International court of Justice, North sea continental Shelf cases, Opcit. (note 7), pp.43-44 && 76-77 (the court found that states that had delimited their continental shelf on the basis of the equidistance principle had not done so because they felt obliged to); ILA report, op.cit.(note 13), principle 17(iv) and Commentary.

በርካታ ደምቦች መታቀብን በሚጠይቁበት አለምአቀፍ የሰብአዊነት ህግ ውስጥ ድርጊቶችን አለመፈፀም የህግ አስተያየት ለመገምገም በሚደረግ ሂደት ላይ የተለየ ችግር ይፈጥራሉ። ለዚህም ምክንያቱ መታቀቡ የተከሰተው በአጋጣሚ ሣይሆን በህጋዊ ሁኔታ በሚጠበቅ ሁኔታ ምክንያት መሆኑ መረጋገጥ ስላለበት ነው። እንደዚህ አይነት መታቀብ እንደሚያስፈልግ በአለምአቀፍ ሰነዶችና በኦፊሴላዊ መግለጫዎች ላይ ሲጠቆም ከተጠቀሰው ባህሪይ ለመታቀብ ያለው ህጋዊ አስፈላጊነት ብዙውን ጊዜ ሊረጋገጥ ይችላል። በተጨማሪም የተጠቀሠው ባህርይ በተወሰነ መልኩ አከራካሪ ሲሆን እንደዚህ አይነት መታቀብ ሊከሰት የሚችል ሲሆን ይህም ምንም እንኳን መታቀቡ የተከሰተው በህጋዊ የሀላፊነት ስሜት ምክንያት መሆኑን ማረጋገጥ ሁልጊዜ ቀላል ባይሆንም መታቀቡ የአጋጣሚ እንዳልሆነ ለማየት ይረዳል።

## የስምምነት ህግ የሚያሣርፈው ጫና (impact)

ስምምነቶችም ልማዳዊ አለምአቀፍ ህግ መኖሩን ለማወቅ በሚደረግ ጥረት ጠቃሚ ናቸው። ምክንያቱም ሀገሮች የተወሰኑ የአለም አቀፍ ህግ ደምቦችን እንዴት እንደሚመለከቷቸው ለማሣየት ስለሚረዱ ነው። ስለዚህም የስምምነት ማፅደቅ፣ አተረጓጎምና አተገባበር እንደዚሁም በማፅደቅ ሂደቱ ወቅት የነበሩ መቆጠቦችና የተሰጡ የአተረጓጎም መግለጫዎች በጥናቱ ውስጥ ተካትተዋል። በNorth Sea Continental Shelf cases ውስጥ አለምአቀፉ ፍርድ ቤት ስምምነቱ የፀደቀበት መጠን ለልማዳዊ አለምአቀፍ ህግ ግምገማ አስፈላጊ ነው በሚል እንዳጤነው ግልፅ ነው። በዚያ ጉዳይ ውስጥ ፍርድ ቤቱ እንዳስቀመጠው በተለይ ከስምምነቱ ውጭ ያለው አሠራር የሚጋጭ በሆነበት ሁኔታ "እስከ አሁን የተገኘው የማፅደቅና የመጨመር (accession) ቁጥር [39] አክብሮት የሚገባው ቢሆንም በቂ ነው ማለት አይቻልም።"[23] በአንፃሩም በኒካራጉዋው ጉዳይ ጣልቃ

---

[23] International Court of Justice, North Sea Continental Shelf cases, op.cit. (note 7,) p.42, & 73

ያለመግባት ደምብ ያለውን የልማዳዊነት ቦታ በሚገመግምበት ወቅት ፍርድ ቤቱ ትልቅ አፅንኦት የሠጠው የተባበሩት መንግስታት ቻርተር አለም አቀፍ ሊባል በሚችል ደረጃ መፅደቁን ነው።[24] በተለይ የተጎዱ ሀገሮችን ጨምሮ በቂ ተመሣሣይ አሠራር ካለና የተጠቀሠውን ደምብ በተመለከተ ብዙ ተቃውሞ የሚቀርብበት ዕድል አነስተኛ ከሆነ የስምምነት ድንጋጌ ልማዳዊ ህግን የሚያንፀባርቅበት ሁኔታም ሊኖር ይችላል።[25]

በተግባር ሲታይ የስምምነት ደምቦችን (norms) ማርቀቅ የአለም የህግ አስተያየቶችን አቅጣጫ ለማስያዝ የሚረዳ ሲሆን ተከትለው በሚመጡ የመንግስታት ባህሪይ እና የህግ እምነት (conviction) ላይ ሊካድ የማይችል ተፅእኖ አለው። አለምአቀፉ ፍርድ ቤት በ continental Shelf Case ብይኑ ውስጥ ለዚሁ ነጥብ ዕውቅና ሰጥቷል። በብይኑ ውስጥ እንዳስቀመጠው "ብዙ ወገኖችን ያካተቱ ስምምነቶች ከልማድ ለሚመነጩ ደምቦች ለመመዝገብና ፍቺ ለመስጠት ወይም ለማሣደግ የሚያስችል ጠቃሚ ሚና ሊኖራቸው ይችላል።[26] ስለዚህ ፍርድ ቤቱ እንዳረጋገጠው ስምምነቶች ቀደም ሲል የነበረን ልማዳዊ አለም አቀፍ ኮድ ሊሰጡት ይችላሉ። በተጨማሪም ግን በስምምነቶቹ ውስጥ በተካተቱት ልሣዶች ላይ ተመርኩዘው አዳዲስ ልማዶች እንዲፈጠሩ መሠረት ሊጥሉ ይችላሉ። ፍርድ ቤቱም "እጅግ ስፋት ያለው እና ወኪል የሆነ በስምምነት

[24] International court of Justice, case concerning Military and Paramilitary Activities in and against Nicaragua, OP.cit. (Note 12), pp.99.100& 188. Another important factor in the decision of the court was that relevant UN General Assembly resolutions had been widely approved, in particular Resolution 2625(xxv) on friendly relations between states which adopted without a vote.

[25] International Court of Justice, Continental shelf case, op cit (note G). p.33,& 34 (the court considered that the concept of an excessive economic zone had become part of the customary international law, even though the United Nations convention on the Law of the sea had not yet entered into force, because the number of claims to an exclusive economic zone had risen to 56,which included several specially affected states.)

[26] International Court of Justice, Continental Shelf case, op.cit.(note 6), pp.29-30, & 27

ላይ የሚደረግ ተሳትፎ ፍላጎታቸው በተለይ የተነካባቸውን ሀገሮች ካካተተ በራሱ በቂ ሊሆን ይችላል፡፡»[27] እስከማለት ሄዶ ነበር፡፡

ጥናቱ የስምምነት በስፋት መፅደቅ ጠቋሚ ብቻ ስለሆነ በአሠራር ውስጥ ካሉ ሌሎች ነጥቦች በተለይም የተጠቀሠው ስምምነት ፈራሚ ያልሆኑ ሀገሮች ካላቸው አሠራር አኳያ መምገም አለበት በሚል ነጥቡን በጥንቃቄ ተመልክቶታል፡፡ የስምምነቱ ፈራሚ ያልሆኑ ሀገሮች ያላቸው ወጥነት ያለው አሠራር እንደ አዎንታዊ ማስረጃ ታይቷል፡፡ ተፃራሪ የሆነ የስምምነቱ ፈራሚ ያልሆኑ ሀገሮች ያላቸው አሠራር የስምምነቱ ፈራሚ ያልሆኑ ሀገሮች ካላቸው አሠራር ጋር ሲተያይ በተለይ ጠቀሜታ አለው፡፡

ስለዚህ ጥናቱ አግባብነት ያላቸውን አለምአቀፍ የሠብአዊነት ህግ ስምምነቶችን ያልፈረሙ ሀገሮች ባላቸው አሠራሮች ላይ አልተወሰነም፡፡ ተጨማሪ ፕሮቶኮሎቹን ያፀደቁ 30 አካባቢ የሚሆኑ ሀገሮች ያላቸውን አሠራር በማየት ብቻ ጥናቱን መገደብ ልማዳዊ አለምአቀፍ ህግ ስፋት ባለው እና ወካይ በሆነ አሰራር ላይ መመስረት አለበት የሚለውን መስፈርት አለማሟላት ይሆናል፡፡ ስለዚህ የልማዳዊ ህግ መኖርን ለማወቅ የተደረገው ግምገማ ጥናቱ ለህትመት በበቃበት ወቅት ተጨማሪ ፕሮቶኮል I በ162 ሀገሮች ተጨማሪ ፕሮቶኮል II ደግሞ በ157 ሀገሮች መፅደቃቸውን ከግምት ውስጥ አስገብቷል፡፡

አፅንኦት ሊሠጠው የሚገባው ጥናቱ እያንዳንዱ የአለምአቀፍ ህግ የስምምነት ደምብ ያለውን ልማዳዊ ባህርይ ለማወቅ ጥረት እንዳላደረገ በዚህም ምክንያት ያሉት ስምምነቶች ያላቸውን አወቃቀር የግድ እንዳልተከተለ ነው፡፡ በምትኩ ለማድረግ የሞከረው ነጥቦችን በመተንተን ከእነዚህ ነጥቦች ጋር ግንኙነት ባለው

27 International Corut of Justice, North Sea Continental Shelf cases, op.cit.(note 7), p.42,& 73; see also ILA Report, op.cit. (note 13), Principles 20-21, 24,26, and 27,pp.754-765.

የሀገር አሠራር ላይ በመመርኮዝ ምን አይነት የልማዳዊ አለምአቀፍ ህግ ደምቦችን መምዘዝ ይቻላል የሚለውን መመለስ ነው፡፡ ለጥናቱ የተመረጠው አካሄድ እያንዳንዱ የስምምነት ድንጋጌ ልማዳዊ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለማወቅ ትንታኔ ስለማይሰጥ ማንኛውም የስምምነት ደምብ በጥናቱ ውስጥ በዚህ መልኩ ስላልቀረበ ብቻ ልማዳዊ አይደለም ከሚል ድምዳሜ ላይ መደረስ የለበትም፡፡

## የጥናቱ አደረጃጀት

የዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል *ኮሚቴ* የተሰጠውን ህጋዊ ስልጣን ለመወጣት እጅግ በጣም ጥሩ የሆነውን መንገድ ለማወቅ እንዲረዳቸው ፀሀፊዎቹ አንድ በአለምአቀፍ የሰብአዊነት ህግ የአካዳሚ ኤክስፖርቶች ቡድንን ያማክሩ የነበረ ሲሆን የኤክስፐርቶቹ ቡድንም የጥናቱ ተቆጣጣሪ (steering) ኮሚቴ ነበር፡፡[28] ይህ ኮሚቴ እ.ኤ.አ. በጁን 1996 ዓ.ም. የስራ ዕቅዱን ያፀደቀ ሲሆን ምርምሩም በቀጣዩ የኦክቶበር ወር ተጀምሯል፡፡ ምርምር የተካሄደው ብሔራዊ እንዲሁም አለም አቀፍ ምንጮችን በመጠቀም ሲሆን ምንጮቹም ሀገራዊ አሠራርን የሚያንፀባርቁ ሲሆኑ በጥናቱ የተለዩት ስድስት ክፍሎች ላይ ያተኮሩ ነበሩ፡፡ ስድስቱ ክፍሎች የሚከተሉት ነበሩ፡፡

- ለይቶ የመመልከት መርህ
- በተለይ የሚጠበቁ ሰዎችና ንብረቶች
- ተወስነው የተለዩ ጦርነት የማካሄጃ ዘዴዎች
- የጦር መሣሪያዎች
- የሲቪሎችና የጦር ጉዳተኞች አያያዝ
- አተገባበር

---

[28] ተቆጣጣሪ ኮሜቴው ያካተታቸው ኘሮፌሰሮች፡- ጆርጅስ አቢ- ሳብ፣ ሳሳህ ኤል-ዲን አመር፣ ኦቬ ብሪንግ፣ ኤሪክ ዴቪድ፣ ጆን ዱጋርድ፣ ፍሎሬንቲኖ ፌሊቺያኖ፣ ሆርስት ፊሸር፣ ፍራንሷ ሀምኘሰን፣ ቴኦዶር ሜሮን፣ ጃምቺድ መምታዝ፣ ሚላን ሳሆቪች እና ራኡል ሚሊዮ ቪኑዌሳ ነበሩ፡፡

## የብሔራዊ ምንጮች ውስጥ የተደረገ ምርምር

ብሔራዊ ምንጮች ይበልጥ በቀላል መንገድ ሊገኙ የሚችሉት ከሀገር ውስጥ ስለሆነ ብሔራዊ ተመራማሪዎችን ትብብር ለመጠየቅ ተወስኖ ነበር፡፡ ለዚህም ሲባል 50 ከሚደርሱ ሀገሮች 9 በአፍሪካ፣ 11 በአሜሪካዎቹ (the Americas)፣ 15 በእስያ፣ 1 በአውስትራሌዢያ (Australasia) ፣ እና 11 በአውሮፓ የሚገኙ ግለሰብ ተመራማሪ ወይም የተመራማሪዎች ቡድን ተመርጠው እነርሱም የየሀገሮቻቸውን አሠራር በተመለከተ ሪፖርት እንዲያዘጋጁ ተጠይቀው ነበር፡፡[29] ሀገሮች የተመረጡት በጂኦግራፊያዊ ውክልና እንዲሁም የተለያዩ የጦርነት ማካሄጃ ዘዴዎች በጥቅም ላይ የዋሉባቸው የተለያዩ የጦር ግጭቶችን በተመለከተ ባላቸው የቅርብ ጊዜ ልምድ ነበር፡፡

የሀገሮች አሠራሮችን አስመልክተው በቀረቡት ሪፖርቶች ውስጥ ሽፋን ያላገኙ የሀገሮች ወታደራዊ መመሪያዎችና ብሔራዊ ህጎችም በምርምር ተሰብስበዋል፡፡ ይህን የማድረጉ ስራ የተቀላጠፈው ዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል በዓለም ዙሪያ ባሉት የልዑክ ፅ/ቤቶች የግንኙነት መረብ እንደዚሁም የዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል የምክር አገልግሎት አለምአቀፍ የሠብአዊነት ህግን በተመለከተ ባለው ሰፊ የብሔራዊ ህጎች ስብስብ አማካኝነት ነበር፡፡

## በዓለም አቀፍ ምንጮች ውስጥ የተደረገ ምርምር

ከዓለም አቀፍ ምንጮች የተለቀሙት የሀገራት አሠራሮች የተሰባሰቡት እያንዳንዳቸው በጥናቱ አንድ ክፍል ላይ ባተኮሩ ስድስት ቡድኖች ነበር፡፡[30] እነዚህ

---

[29] ከአፍሪካ፡- አልጄሪያ፣ አንጎላ፣ ቦትስዋና፣ ግብፅ፣ ኢትዮጵያ፣ ናይጄሪያ፣ ሩዋንዳ፣ ደቡብ አፍሪካና ዚምባቡዌ፡፡ ከአሜሪካዎቹ፣- አርጀንቲና፣ ብራዚል፣ ካናዳ፣ ቺሊ፣ካምቦዲያ፣ ኩባ፣ ኤልሳልቫዶር፣ ሪካራጉዋ፣ፔሩ፣ ዩኤስ አሜሪካና ኡራጉዋይ፡፡ ከእስያ፡- ቻይና፣ ህንድ፣ ኢንዶኔዢያ፣ ኢራን፣ኢራቅ፣እስራኤል፣ ጃፓን፣ዮርዳኖስ፣ የኮሪያ ሪፐብሊክ፣ኩዌት፣ሊባኖስ፣ማሌዢያ፣ፓኪስታን፣ፊሊፒንስና ሶሪያ፡፡ ከውስትራሌዢያ፡- አውስትራሊያ፡፡ ከአውሮፓ፡- ቤልጂየም፣ ቦስኒያና ሄርዞጎቪና፣ክሮኤሺያ፣ፈረንሳይ፣ጀርመን፣ጣሊያን፣ኔዘርላንድስ፣የራሺያ ፌዴሬሽን፣ስፔን፣እንግሊዝና ዩጎዝላቪያ፡፡

[30] የመለያ መርህ፡- ኘሮፌሰር ጆርጅስ አቢ-ሳብ(ራፖ`ርተር)እና ዣን-ፍራንሷ ኩዌጉዊነር (ተመራማሪ)፡፡ በተለይ የሚጠበቁ ሰዎችና ዕቃዎች፡-ኘሮፌሰር ሆርስት ፊሸር (ራፖ`ርተር)እና ግሬጎር ሾተንና ሀይክ ስፓይከር

ቡድኖች አሠራርን በተመለከተ ምርምር ያካሄዱት በተባበሩት መንግስታትና እንደየአፍሪካ ህብረት (የቀድሞ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት) ፣ የአውሮፓ ምክር ቤት፣ የገልፍ የትብብር ጉባኤ፣ የአውሮፓ ህብረት፣ የአረብ ሀገሮች ሊግ፣ የአሜሪካ ግዛቶች ድርጅት፣ የእስላማዊ ጉባኤ ድርጅት እና የአውሮፓ የደህንነትና ትብብር ድርጅት ባሉ አለምአቀፍ ድርጅቶች ማዕቀፍ ውስጥ ሆነው ነበር። ዓለምአቀፍ የጉዳይ ህግም (case-law) እንደዚሁ የልማዳዊ አለምአቀፍ ህግ ደምቦች መኖርን የሚያሣይ መረጃ እንዲሰጥ በሚል ተሰባስቦ ነበር።

## በዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ ቤተ መዛግብት ውስጥ የተደረገ ምርምር

በብሔራዊና አለምአቀፍ ምንጮች ውስጥ የተደረገውን ምርምር ለማገዝ በማሠብ ዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል በራሱ ቤተ መዛግብት (archives) ውስጥ የሚገኙ በቅርብ ጊዚያት የተደረጉ 40 የሚደርሱ (በአፍሪካ 21፣ በአሜሪካዎቹ 2፣በእስያ 8 እና በአውሮፓ 8) የጦር ግጭቶች መዝገቦችን መርምሯል።[31] በአጠቃላይ እነዚህ ግጭቶች የተመረጡት በሀገር አሠራር ሪፖርት ያልተዳሰሱ ሀገሮችና ግጭቶች ሽፋን እንዲያገኙ ነው።

ሶስት ዘርፎች ያሉት የዚህ አሠራር (በብሔራዊ፣ በአለም አቀፍና በየዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ምንጮች ውስጥ የተደረጉ ምርምሮች) ውጤት በሁሉም የዓለም

(ተመራማሪዎች)። ተወስነው የተለዩ ጦርነት የማካሄጃ ዘዴዎች፡-ኘሮፌሰር ቴዎዶር ሜሮን (ራፖርተር)እና ሪቻርድ ዴስጋኜ (ተመራማሪ)። የጦር መሣሪያዎች፡-ኘሮፌሰር ኦቬ ብሪንግ (ራፖርተር)እና ጉስታፍ ሊንድ (ተመራማሪ)፡የሲቪሎችና የጦር ጉዳተኞች አያያዝ፡-ፍራንሷ ሃምኘሰን (ራፖርተር)እና ካሚል ጂፋርድ (ተመራማሪ)። አተገባበር፡-ኤሪክ ዴቪድ (ራፖርተር)እና ሪቻርድ ዴስጋኜ (ተመራማሪ)

31 በአፍሪካ፡- አንጎላ፣ቡሩንዲ፣ቻድ፣ቻድ-ሊቢያ፣ኮንጎ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ፣ጂቡቲ፣ኤርትራ- የመን፣ ኢትዮጵያ (1973-1994)፣ ላይቤሪያ፣ ሞዛምቢክ፣ናሚቢያ፣ናይጄሪያ-ካሜሩን፣ሩዋንዳ፣ ሴኔጋል፣ሴኔጋል-ሞሪታኒያ፣ሴራሊዎን፣ሶማሊያ፣ሶማሊያ-ኢትዮጵያ፣ሱዳን፣ኡጋንዳና ምዕራብ ሰሀራ። በአሜሪካዎቹ፡-ጉዋቲማላና ሜክሲኮ። በእስያ፡- አፍጋኒስታን፣ ካምቦዲያ፣ህንድ(ጃሙና ካሽሚር)፣ፓርዋኒው ጊኒ ሽሪላንካ፣ታጂኪስታን፣የመን፣የመን-ኤርትራ (በአፍሪካ ውስጥም የታየ)። በውሮፓ፣- አርሜኒያ-አዘርባይጃን(ናጎርኖ ካራባህ)፣ቆጵሮስ፣ የቀድሞዋ ዩጎዝላቪያ(በዩጎዝላቪያ ውስጥ የነበረ ግጭት(1991-1992)፣ በቦስኒያና ሄርዞጎቪና የነበረ ግጭት (1991-1992)፣ በቦስኒያና ሄርዞጎቪና የነበረ ግጭት (1992-1996)፣ በክሮኤሺያ የነበረ ግጭት (ክራይናስ)(1992-1995)፣ጆርጂያ (አብካዚያ)፣የራሺያ ፌዴሬሽን (ቼችኒያ) እና ቱርክ።

ክፍሎች ያለ አሠራር መጠቀሱ ነው፡፡ ነገር ግን በነገሮች ባህሪያት ምክንያት ይህ ምርምር የተሟላ ነው ማለት አይቻልም፡፡ ውጤቱ ወቅታዊ የሆነውን ልማዳዊ አለምአቀፍ ህግ መልሶ የሚያቀርብ መሆኑን ለማረጋገጥ ጥናቱ በተለይ ያተኮረው ባለፉት 30 ዓመታት ያለ አሰራር ላይ ሲሆን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ግን ከዚህም የሚበልጥ ዕድሜ ያለው አሠራር ተጠቅሷል፡፡

## ከኤክስፐርቶች ጋር የተደረገ መመካከር

በመጀመሪያው ዙር ምክክር ወቅት ዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል አለምአቀፍ የምርምር ቡድኖቹ የተሰበሰበው አሠራር ላይ በመመርኮዝ ልማዳዊ አለምአቀፍ የሰብአዊነት ህግ የመጀመሪያ ግምገማን የያዘ (executive) ማጠቃለያ እንዲያዘጋጁ ጋብዟል፡፡ እነዚህ ማጠቃለያዎች በ1998 ዓ.ም በጄኔቫ ውስጥ በተደረጉ የጥናቱ ተቆጣጣሪ ኮሚቴ ስብሰባዎች ውስጥ ውይይት ተደርጎባቸዋል፡፡ ማጠቃለያዎቹም በሚገባ ከታዩና ከተስተካከሉ በኋላ በሁለተኛው ዙር ምክክር ወቅት ከሁሉም የአለም ክፍሎች ለተውጣጣ አካዳሚያዊና የመንግስት ኤክስፐርት ቡድን ቀርበዋል፡፡ እነዚህ ኤክስፐርቶች በ1999 ዓ.ም. በጄኔቫ የተደረጉ ሁለት የተቆጣጣሪው ኮሚቴ ስብሰባዎች ላይ እንዲካፈሉ በዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ የተጋበዙት በግለሰብ ደረጃ ሲሆን በስብሰባዎቹ ውስጥም የተሰበሰቡትን አሠራሮች በመገምገም፣ ያልተካተቱ አሠራሮችን በመጠቆም ረድተዋል፡፡[32]

---

[32] የሚከተሉት የአካዳሚ እና የመንግስት ኤክስፐርቶች በዚህ ምክክር ውስጥ በግላቸው ተሳትፈዋል፡፡ አብደላ አድ-ዱሪ(ኢራቅ)፣ፖል በርማን (እንግሊዝ)፣ሰዲ ሳይሊ (ቱርክ)፣ማይክል ኮውሊንግ (ደቡብ አፍሪካ)፣ኤድዋርድ ኩሚንግስ (ዩኤስ አሜሪካ)፣አንቶኒዮ ዴኢካዛ (ሜክሲኮ)፣ዮራም ዲንስታይን(እስራኤል)፣ዣን-ሚሼል ፋብር (ፈረንሳይ)፣ ዊሊያም ፌንሪክ(ካናዳ)፣ዳይተር ፍሌክ(ጀርመን)፣ሁዋን ካርሎስ ጎሜዝ ራሚሬዝ (ኮሎምቢያ)፣ ጃምሼድኤ.ሀሚድ(ፓኪስታን)፣ አርቱሮ ሄርናንዴዝ በጎብ(ሜክሲኮ)፣ኢብራሂም ኢድሪስ (ኢትዮጵያ)፣ሀሠን ቃሲም ጂኒ(ሊባኖስ)፣ኬኔት ኪት(ኒው ዚላንድ)፣ጊቱ ሙይጋይ(ኬኒያ)፣ራይን ሙለርሰን(ኢስቶኒያ)፣ባራ ኒያንግ (ሴኔጋል)፣ሞሀመድ ኦልዋን(ዮርዳኖስ)፣ ራኢል ሊ. ፓንጋላንጋን (ፊሊፒንስ)፣ ስቴሊዮስ ፔራሲስ (ግሪክ)፣ ፓውሎ ሰርጂዮ ፒኔሪዮ (ብራዚል)፣አርፖድ ኘራንድለር(ሀንጋሪ)፣ፔምራጁ ስሪኒቫሳ ራኦ(ህንድ)፣ ካሚሎ ሬዩስ ሮድሪጉዌዝ (ኮሎምቢያ)፣ኢትሴኢ.ሳጋይ (ናይጄሪያ)፣ ሀሮልድሳንዶቫል (ኮሎምቢያ)፣ሳምቡን ሳንጂያንቡት (ታይላንድ)፣ማራት ኤ.ጎርሴምባዬብ (ካዛክስታን)፣ሙሀመድ አዚዝ ሹክሪ(ሶሪያ)፣ፓርሎንጋን ሲሆምቢንግ (ኢንዶኔዢያ)፣ጄኦፍሪ ጀምስ ስኬሰን (አውስትራሊያ)፣ጉሸን ሰን(ቻይና)፣ባክትያር ቱዝሙካሜዶብ (ራሺያ) እና ካሮልዎልፍክ(ፖላንድ)፡፡ራኢልሲ.ፓንጋላንጋን(ፊሊፒንስ)፣ስቴሊዮስ ፔራኪስ (ግሪክ)፣ፓውሎ ሰርጂዮ ፒኔሪዮ (ብራዚል)፣አርፓድ ኘራንድለር(ሀንጋሪ)፣ፔማራጁ ስሪኒቫሳ ራኦ(ህንድ)፣ካሚሎ ሬዩስ ሮድሪጉዌዝ (ኮሎምቢያ)፣ ኢትሴኢ.ሳጋይ(ናይጄሪያ)፣ሀሮልድ ሳንዶቫል(ኮሎምቢያ)፣ሳምቡን ሳንጁያንቡት (ታይላንድ)፣ማራት

## ሪፖርቱን መጻፍ

የተቆጣጣሪ ኮሚቴው ግምገማና በአካዳሚና በመንግስት ኤክስፐርቶች ቡድን የተሰጠው አስተያየት የተጠናቀቀውን ሪፖርት ለመፃፍ የሚያስችል መሠረት በመጣል አገልግለዋል፡፡ የጥናቱ ፀሀፊዎች አሠራሩን በድጋሚ ፈትሸዋል፣ የልማድ መኖርን በድጋሚ ገምግመዋል፣ የደምቦቹን አመሠራረትና ቅደም ተከተል በድጋሚ ተመልክተዋል እንዲሁም አስተያየቶቹን አርቅቀዋል፡፡ እነዚህ ረቂቆችም ለተቆጣጣሪው ኮሚቴ ፣ ለአካዳሚና የመንግስት ኤክስፐርቶች ቡድንና ለዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ የህግ ክፍል አስተያየት እንዲሰጥባቸው ቀርበዋል፡፡ ከዚያም የተሰጡትን አስተያየቶች ከግምት ውስጥ በማስገባት ፅሁፉ ተሻሽሎ ተጠናቅቋል፡፡

## ግኝቶች በተጠቃለለ መልኩ

የጋራ አንቀፅ 3ን ጨምሮ አብዛኛዎቹ የጄኔቫ ስምምነቶች ድንጋጌዎች የልማዳዊ አለምአቀፍ ህግ አካላት ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡[33] በተጨማሪም በአሁኑ ወቅት የጄኔቫ ስምምነቶችን የፈረሙ 192 ሀገሮች አሉ፡፡ ስምምነቶቹም እንደ የስምምነት ህግ በሁሉም ሀገሮች ላይ ማለት ይቻላል አሣሪነት አላቸው፡፡ ስለዚህ የስምምነቶቹ ድንጋጌዎች ልማዳዊ ባህርይ አላቸው ወይ የሚለው በራሱ የጥናቱ ርዕስ አልነበረም፡፡ በምትኩ ጥናቱ ያተኮረው በአለም አቀፍ ደረጃ ስለፀደቁ ስምምነቶች በተለይ ተጨማሪ ፕሮቶኮሎቹ፣ የሔግ የባህላዊ ንብረት ጥበቃ

ኤ.ሳርሴምባዬቭ (ካዝክስታን)፣ሙሀመድ አዚዝ ሹክሪ (ሶሪያ)፣ፓርሎንጋን(ፊሊፒንስ) ሲሆምቢንግ (ኢንዶኔዢያ)፣ ጄኦፍሪ ጄኦፍሪ ጀምስ ስኪለን (አውስትራሊያ)፣ ጉሽን ሰን (ቻይና)፣ባክትያር ቱዝሙካ ሜዶቭ (ራሺያ) እና ካርል ዎልፍክ(ፖላንድ)፡፡

[33] International Court of Justice, Legality of the Threat or Use of Nuclear Weapons, OP.cit.(note8.),pp.257,288, 79 and 82 (with respect to the General Conventions) and case concerning Military and Paramilitary Activities in and against Nicaragua, op.cit.(note 12),p.114 &218(with respect to common article 3).

ስምምነት እና ሌሎች የጦር መሣሪያ አጠቃቀም ሥርዐትን የተመለከቱ ስምምነቶች ስርዐት ባበጁላቸው ጉዳዮች ላይ ነበር።

ከዚህ በታች የቀረበው የልማዳዊ አለምአቀፍ ህግ ደምቦች ገለፃ እነዚህ ደምቦች ለምን ልማዳዊ ሆነው እንደተገኙ ለማብራራት አይሞክርም። እንደዚሁም ከዚህ መደምደሚያ ላይ ለመድረስ መሠረት የሆነውን አሠራርም አያቀርብም። አንድ ደምብ ለምን ልማዳዊ ተብሎ እንደሚወሰድ የሚያሣይ ማብራሪያ በጥናቱ ቅፅ I ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ተዛማጁ አሠራር ደግሞ በቅፅ II ውስጥ ይገኛል።

## አለም አቀፍ የጦር ግጭቶች

ተጨማሪ ኘሮቶኮል I ቀደም ሲል ለነበሩ የልማዳዊ አለም አቀፍ ህግ ደምቦች ኮድ የሰጣቸው ሲሆን በተጨማሪም አዳዲስ ልማዳዊ ደምቦች እንዲፈጠሩ መሠረት ጥሏል። በጥናቱ ማዕቀፍ ውስጥ የተሰባሰበው አሠራር እንደመሠከረው ተጨማሪ ኘሮቶኮል I በሀገሮች አሠራር ላይ ትልቅ ተፅእኖ ያሳርፋል። ይህም በአለምአቀፍ የጦር ግጭቶቹ ውስጥ ብቻ ሳይሆን አለም አቀፍ ባልሆኑ የጦር ግጭቶችም ውስጥ ነው (ከታች ተመልከት)። በተለይም በጥናቱ ግኝት መሠረት የተጨማሪ ኘሮቶኮል I መሠረታዊ መርሆች ተጨማሪ ኘሮቶኮል I የፀደቀበት መዝገብ ከሚጠቁመው በበለጠ ስፋት ተቀባይነት አላቸው።

ምንም እንኳን ጥናቱ የተወሰኑ የስምምነት ድንጋጌዎች ያላቸውን ልማዳዊ ባህርይ የማወቅ አላማ ያልነበረው ቢሆንም በመጨረሻ ግልፅ የሆነው በስምምነት ህግ ውስጥ ከሚገኙት ደምቦች ጋር አንድ አይነት ወይም ተመሣሣይ የሆኑ በርካታ ልማዳዊ ደምቦች እንዳሉ ነው። ልማዳዊ ሆነው የተገኙና ከተጨማሪ ኘሮቶኮል I ውስጥ ተጓዳኝ ድንጋጌዎች ካሏቸው ደምቦች ውስጥ ለምሣሌ ፦ ሲቪሎችንና ተዋጊዎችን እንዲሁም ሲቪል ዕቃዎችንና ወታደራዊ ኢላማዎችን

ለያይቶ የመመልከት መርህ[34] ዒላማን ያልለየ አጠቃላይ ጥቃት መከልከል[35]፣ የተመጣጣኝ ጥቃት መርህ፣[36] በማጥቃትና ለጥቃት ምላሽ በመስጠት ወቅት አስፈላጊ ጥንቃቄ የማድረግ ግዴታ[37]፣ የህክምናና የሀይማኖት ሠራተኞችን፣ የህክምና ክፍሎችና መገናኛዎችን[38] ፣ የሠብአዊ እርዳታ ሠራተኞችንና ንብረታቸውን[39]፣ እንዲሁም ሲቪል ጋዜጠኞችን[40] የማክበርና የመጠበቅ ግዴታ፣ የህክምና ተግባራትን የመጠበቅ ግዴታ[41]፣ ጥበቃ በማይደረግላቸው ሠፈሮችና ከወታደራዊ እንቅስቃሴ ነፃ የሆኑ ቀጠናዎችን የማጥቃት መከልከል[42] ፣ በጦርነት ጉዳት ለደረሰባቸው የጠላት ወገኖች መጠለያ እና ጥበቃ የማቅረብ ግዴታ[43]፣ የማስራብ መከልከል[44] ፣ ለሲቪሉ ህዝብ በህይወት መቆየት የግድ አስፈላጊ በሆኑ ንብረቶች ላይ የሚደረግ ጥቃት መከልከል[45] ፣ አርማዎችን ያለአግባብ መጠቀምና የሸፍጥ ድርጊት ክልከላ፣[46] ሲቪሎችና በጦርነት የተጎዱ ሰዎች ያሏቸውን መሠረታዊ ዋስትናዎች የማክበር ግዴታ፣[47] የጠፉ ሰዎች ያሉበትን ቦታ የማወቅ ግዴታ፣[48] እና ሴቶችና ህፃናት ያሏቸው የተለዩ ጥበቃዎችን[49] መጥቀስ ይቻላል፡፡

## ዓለም አቀፍ ያልሆኑ የጦር ግጭቶች

---

34 See Customary International Humanitarian Law, op.cit(note 4), vol I, Rules 1 and 7
35 ,lbid.,Rules 11-13
36 Ibid., Rules 14
37 Ibid., Rules 15-24
38 Ibid., Rules 25 and 27-30
39 Ibid., Rules 31-32
40 Ibid., Rules 34
41 Ibid., Rules 26
42 Ibid., Rules 36-37
43 Ibid., Rules 46-48
44 Ibid., Rules 53
45 Ibid., Rules 54
46 Ibid., Rules 57-65
47 Ibid., Rules 87-105
48 Ibid., Rules 117
49 Ibid., Rules 134-137

ባለፉት ጥቂት አስርት አመታት በእንደዚህ አይነት ግጭቶች ውስጥ ለዓለምአቀፍ የሰብአዊነት ህግ መከበር አፅንኦት የሚሠጡ በመጠን በርከት ያሉ አሠራሮች ነበሩ፡፡ ይህ የአሠራር ክምችት አለምአቀፍ ባልሆኑ የጦር ግጭቶች ውስጥ ተፈፃሚ የሚሆን ልማዳዊ ህግ እንዲፈጠር አይነተኛ ተፅዕኖ ነበረው፡፡ ልክ እንደ ተጨማሪ ኘሮቶኮል I ሁሉ ተጨማሪ ኘሮቶኮል II በዚህ አሠራር ላይ ሠፊ ተፅዕኖ የነበረው ሲሆን በተጨማሪም ካሉት ድንጋጌዎች በርካታዎቹ በአሁኑ ወቅት የልማዳዊ አለም አቀፍ ህግ አካላት ተደርገው ይቆጠራሉ፡፡ ለምሣሌ ልማዳዊ ሆነው የተገኙና በተጨማሪ ኘሮቶኮል II ውስጥ ተጓዳኝ ድንጋጌዎች ካሏቸው ደምቦች መካከል በሲቪሎች ላይ የሚደረግ ጥቃት መከልከል[50] ፣ የህክምናና የሀይማኖት ሠራተኞችን፣ የህክምና ክፍሎችና መገናኛዎችን የማክበርና የመጠበቅ ግዴታ[51]፣ የህክምና ተግባራትን የመጠበቅ ግዴታ፣[52] የማስራብ መከልከል፣[53] ለሲቪሉ ህዝብ ህይወት የግድ አስፈላጊ በሆኑ ንብረቶች ላይ የሚደረግ ጥቃት መከልከል፣[54] የሲቪሎችና በጦርነት የተጎዱ ሰዎች ያሏቸውን መሠረታዊ ዋስትናዎች የማክበር ግዴታ፣[55] የቆሰሉ፣ የታመሙና በባህር ላይ አደጋ የደረሰባቸውን ሰዎች የማፈላለግ፣ የማክበርና የመጠበቅ ግዴታ፣[56] የሞቱ ሰዎችን የማፈላለግና የመጠበቅ ግዴታ፣[57] ነፃነታቸውን የተነፈጉ ሰዎችን የመጠበቅ ግዴታ፣[58] ሲቪሎችን በሀይል የማፈናቀል መከልከል፣[59] እና ሴቶችና ህፃናት ያሏቸው የተለዩ ጥበቃዎችን[60] መጥቀስ ይቻላል፡፡

---

[50] Ibid., Rule 1
[51] Ibid., Rules 25 and 27-30
[52] Ibid., Rules 26
[53] Ibid., Rules 53
[54] Ibid., Rules 54
[55] Ibid., Rules 87-105
[56] Ibid., Rules 109-111
[57] Ibid., Rules 112-113
[58] Ibid., Rules 118-119,121 and 125
[59] . Ibid., Rules 129
[60] Ibid., Rules 131-137

ይሁን እንጂ ልማዳዊ አለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግ ለውስጥ የጦር ግጭቶች ስርዐት የሚያበረክተው እጅግ ጠቃሚ አስተዋፅኦ የተጨማሪ ኘሮቶኮል II ድንጋጌዎችን አልፎ መሄዱ ነው፡፡ እርግጥ አሠራር በተጨማሪ ኘሮቶኮል II ውስጥ ከሚገኙትና ብዙውን ጊዜ በደምብ ካልተሟሉት ድንጋጌዎች የበለጠ ዝርዝር የያዙ ቁጥራቸው በርካታ የሆነ ልማዳዊ ደምቦችን ፈጥሯል፡፡ በዚህም ከውስጥ ግጭቶች ስርአት አኳያ የነበሩ ክፍተቶችን በመሙላት ጠቅሟል፡፡

ለምሣሌ ተጨማሪ ኘሮቶኮል II ግጭቶችን ስለማካሄድ የያዛቸው በደምብ ያልተሟሉ መመሪያዎችን ብቻ ነው፡፡ አንቀፅ 13 እንደሚደነግገው "ሲቪሉ ህዝብ እንዳለ እንዲሁም ግለሰብ ሲቪሎች በግጭቶች ውስጥ በቀጥታ እስካልተሳተፉና ከዚህ ሁኔታ ከወጡ የጥቃት ዒላማ መሆን የለባቸውም፡፡" ከተጨማሪ ኘሮቶኮል I በተለየ ሁኔታ ተጨማሪ ኘሮቶኮል II ለይቶ የመመልከትና የተመጣጣኝነት መርሆችን በተለይ የተመለከቱ ያካተታቸው ደምቦችና ፍቺዎች የሉም፡፡

በተጨማሪ ኘሮቶኮል II በተካተተው ግጭቶችን የማካሄድ መመሪያ ውስጥ ያሉት ክፍተቶች ግን በአብዛኛው በሀገራዊ አሠራር በኩል የተሸፈኑ ሲሆን ይህም በተጨማሪ ኘሮቶኮል I ውስጥ ካሉት ደምቦች ጋር ትይዩ የሆኑ ነገር ግን እንደ ልማዳዊ ህግ አለምአቀፍ ባለሆኑ የጦር ግጭቶች ውስጥ ተፈፃሚ የሚሆኑ ደምቦች እንዲፈጠሩ አድርጓል፡፡ ይህም የሚሸፍነው የግጭቶች አካሄድ መሠረታዊ መርሆችን ሲሆን በተለይ የሚጠበቁ ሰዎችና ንብረቶችን የተመለከቱ ደምቦችንና የተወሰኑ ጦርነት የማካሄጃ ዘዴዎችን ያካትታል፡፡[61] በተመሣሣይም ተጨማሪ ኘሮቶኮል II ለተቸገሩ ሲቪል ህዝቦች ሰብአዊ እርዳታ ስለማቅረብ

---

[61] see e.g. ibid., Rules 7-10 (distinction between civilian objects and military objectives), Rules 11-13(Indiscriminate attacks), Rule 14 (proportionality in attack), rules 15-21 (Precaution in attack) Rules 22-24 (Precaution: against the effects of attack);Rules 31-32 (Humanitarian relief personnel and objects), rule 34(Civilian journalists),Rules 35-37(Protected zones), Rules 46-48(denial of quarter),Rules 55-56(access to humanitarian relief) and Rules 57-65(deception)

የያዘው ድንጋጌ በጣም ጠቅላላ ነው፡፡ አንቀፅ 18 (2) እንደሚደነግገው "ሲቪሉ ሕዝብ ለመኖር በሚያስፈልጉት አቅርቦቶች እጥረት ምክንያት አላግባብ እየተሰቃየ ከሆነ --- ሲቪሉ ህዝብን የሚጠቅሙ ፍፁም ሰብአዊና ገለልተኛ ባህሪይ ያላቸው እንዲሁም ያለምንም ማዳላት የሚከናወኑ የእርዳታ እርምጃዎች መወሠድ አለባቸው፡፡" ከተጨማሪ ኘሮቶኮል I በተለየ ሁኔታ ተጨማሪ ኘሮቶኮል II የሰብአዊነት ዕርዳታ ሰራተኞች እንዲከበሩና እንዲጠበቁ የሚጠይቁ ፣ በግጭቱ ተሳታፊ የሆኑ ወገኖች ለተቸገሩ ሲቪሎች የሚሠጠው ሰብአዊ እርዳታ በፍጥነትና ያለእንቅፋት ማለፍ እንዲችል እንዲፈቅዱና ሁኔታዎችን እንዲያመቻቹ የሚያስገድዱ እንዲሁም ምንም እንኳን እንደዚህ አይነት ጥያቄዎች በአንቀፅ 18 (2) ውስጥ በውስጠ ታዋቂነት ተካትተዋል ሊባል ቢችልም ፈቃድ ላላቸው የሰብአዊ እርዳታ ሰራተኞች የመንቀሣቀስ ነፃነታቸውን እንዲያረጋግጡላቸው የሚጠይቁ የተለዩ ድንጋጌዎችን አላካተተም፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ አስፈላጊ ነገሮች ስፋት ባለው፣ ወካይ እና ሙሉ ለሙሉ ወጥ በሆነ አሠራር ምክንያት ቅርፅ ይዘው በአለም አቀፍም ሆነ አለምአቀፍ ባልሆኑ የጦር ግጭቶች ውስጥ ተፈፃሚነት ወዳለው ልማዳዊ አለምአቀፍ ህግነት አድገዋል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ መጠቀስ ያለበት ነጥብ ተጨማሪ ኘሮቶኮል I እና II ሁለቱም የዕርዳታ ስራ ለመስራት የሚመለከታቸው ወገኖች ስምምነትን የሚጠይቁ ቢሆንም[62] አብዛኛው የተሰባሰበ አሠራር ይህንን አይጠቅስም፡፡ ቢሆንም ግን አንድ የዕርዳታ ድርጅት የሚመለከታቸው ወገኖች ስምምነት ከሌለ ስራውን መስራት እንደማይችል በራሱ ግልፅ ነው፡፡ ይሁን እንጂ እንደዚህ አይነት ስምምነት በዘፈቀደ መከልከል የለበትም፡፡ ሲቪል ህዝብ ለረሀብ አደጋ እንደተጋለጠ ከተረጋገጠና በገለልተኛ ሁኔታና ያለማዳለት ዕርዳታ የሚያቀርብ የዕርዳታ ድርጅት ለችግሩ መፍትሄ መስጠት የሚችል ከሆነ ማንኛውም ወገን የመስማማት

[62] See Additional Protocol I, Article 70(1) and Additional Protocol II, Article 18(2)

ግዴታ አለበት፡፡[63] የዘፈቀደ በሆኑ ምክንያቶች ስምምነት የማይከለከል ቢሆንም አሠራር ዕውቅና እንደሚሠጠው የሚመለከተው ወገን የዕርዳታ አሠጣጥ ስራውንና የዕርዳታ ሰራተኞች ድንበር አቋርጠው ሲገቡ የሀገር ውስጥ ህግን እንዲሁም በስራ ላይ ያሉትን ለደህንነት አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ማክበራቸውን መቆጣጠር ይችላል፡፡

## ተጨማሪ ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች

ጥናቱ በተጨማሪ በርካታ አሠራር ግልፅ ያልሆነባቸው ቦታዎችን አሣይቷል፡፡ ለምሣሌ "ተዋጊዎች" እና "ሲቪሎች" የሚሉት ቃላት በአለም አቀፍ የጦር ግጭቶች ውስጥ ግልፅ ፍቺ የተሰጣቸው ቢሆንም[64] አለም አቀፍ ያልሆኑ የጦር ግጭቶች አሠራር (ግጭቱን ለማካሄድ ሲባል) የታጣቂ የተቃዋሚ ቡድን አባላት የሚታዩት እንደ የጦር ሀይል አባላት ነው ወይስ እንደ ሲቪሎች የሚለውን በተመለከተ ግልፅ አይደለም፡፡ በተለይ ግልፅ ያልሆነው ነጥብ የታጣቂ ተቃዋሚ ቡድኖት አባላት በግጭቱ በቀጥታ በመሣተፋቸው ከጥቃት የመጠበቅ መብታቸውን ያጡ ሲቪሎች ናቸው ወይስ የእንደዚህ አይነት ቡድኖች አባላት ሊጠቁ ይችላሉ የሚለው ነው፡፡ ይህ የግልፅነት እጥረት በስምምነት ህግ ውስጥም ተንፀባርቋል፡፡ ለምሣሌ ተጨማሪ ፕሮቶኮል II ሲቪሎች ወይም ሲቪሉ ህዝብ የሚሉት ቃላት በበርካታ ድንጋጌዎች ወስጥ የሚገኙ ቢሆንም ለቃላቱ ምንም ፍቺ አልያዘም፡፡[65] አለም አቀፍ ባልሆኑ የጦር ግጭቶች ወቅት ተፈፃሚነት ያላቸው ቀጥለው የመጡ ስምምነቶችም በተመሣሣይ ሲቪሎች እና ሲቪል ህዝብ የሚሉትን ቃላት ፍቺ ሣይሠጡ ተጠቅመውባቸዋል፡፡[66]

---

[63] See Yves Sandos, Christopher Swinarski, Bruno Zimmenmann (eds.) commentary on the Additional Protocols, ICRC, Genara 1987, & 4885,see also & 2805

[64] See Customary International Humanitarian Law, op.cit.(note.4),Vol.I Rule 3 (combatants), Rule 4(Armed Forces) and Rule 5(Civilians and Civil Population)

[65] Additional Protocol II, Articles 13-15, and 17-18

[66] see, e.g. Amended Protocol II to the Convention on Certain Conventional Weapons, Article 3(7)-

*በተያያዘም አለም አቀፍ እንደዚሁም አለም አቀፍ ያልሆኑ የጦር ግጭቶች ደምቦችን የሚነካ ሌላ ጥርጣሬ ያለው "በግጭቶች ውስጥ በቀጥታ መሣተፍ" ለሚለው አገላለፅ ቁርጥ ያለ ፍቺ አለመኖሩ ላይ ነው፡፡ አንድ ሲቪል የሆነ ሰው የጦር መሣሪያ ወይም ሌላ መንገድ በመጠቀም በጠላት ሀይሎች ላይ በሰው ወይም በንብረት ላይ የሀይል ድርጊቶችን ቢፈፅም ከጥቃት የመጠበቅ መብቱን ያጣል የሚለው ግልፅና የማያከራክር ነው፡፡ ነገር ግን "ቀጥተኛ ተሳትፎ" ለሚለው አገላለፅ ትርጉም የሚሰጥ ምንም መመሪያ የሌለው በርካታ አሠራር አለ፡፡ ለምሣሌ ግምገማው ጉዳዮችን አንድ በአንድ በማየት መከናወን አለበት የሚል ወይም በግጭት ውስጥ ቀጥተኛ ተሣትፎ ማድረግ አንድ ሲቪል ያለውን ከጥቃት የመጠበቅ መብት ያሣጣዋል የሚለውን አጠቃላይ ደምብ ብቻ የሚደግም አለ፡፡ ከዚህ ጉዳይ ጋር በሚገናኝ በጥርጣሬ ወቅት አንድን ሰው እንዴት አድርጎ መግለፅ ይቻላል የሚለው ጥያቄ አለ፡፡ እነዚህን እርግጠኛ መሆን የማይቻልባቸውን ነጥቦች ለመፍታትና የቀጥተኛ ተሣትፎ ፅንሠ ሀሣብን ግልፅ ለማድረግ ዓ.አ.ቀ.መ.ኮ. ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ እየተደረጉ ባሉ ተከታታይ የኤክስፖርቶች ስብሰባዎች አማካኝነት ጥረት እያደረገ ነው፡፡*[67]

*አሁንም ለጥያቄ ክፍት የሆነ ጉዳይ የጥቃት ተመጣጣኝነት መርህ በትክክል የሚሸፍነው ምንን ነው አፈፃፀሙስ እንዴት ነው የሚለው ነው፡፡ ጥናቱ ይህ መርህ ሠፊ ድጋፍ እንዳለው ያሣየ ቢሆንም በስምምነት ህግ ውስጥ ከሚገኘው*

(11);Protocol III to the convention on Certain Conventional Weapons, Article 2; Ottawa Convention on the Prohibition of Anti-Personnel Mines, Preamble; Statute of the International Criminal Court, Article 8(2)(e)(i),(iii) and (viii).

[67] See, e.g. Direct Participation in Hostilities under International Humanitarian Law, Report Prepared by the ICRC, Genera, September 2003,available on www. icrc. org.

ሌላ እንዴት ወታደራዊ ጥቅምን ከድንገተኛ የሲቪል ኪሣራዎች ጋር ማመጣጠን እንደሚቻል የሚያቀርበው የበለጠ ማብራሪያ የለም፡፡

## የጦር ግጭቶችን ማካሄድን በተመለከተ የተመረጡ ጉዳዮች

ተጨማሪ ኘሮቶኮል I እና II አደገኛ ሀይሎችን በያዙ ህንፃዎች ላይ የሚደረግ ጥቃትን በተመለከተ የሚደረገው ጥቃት አደገኛ ሀይሎቹ አምልጠው እንዲወጡ የሚያደርግና በውጤቱም በሲቪሉ ህዝብ ላይ ከፍተኛ ኪሣራ የሚያስከትሉ ከሆነ ህንፃዎቹ ወታደራዊ ኢላማዎች ቢሆኑ እንኳን ጥቃቱን የሚከለክል አዲስ ደምብ አስቀምጠዋል፡፡[68] እነዚህ ደምቦች የልማዳዊ ህግ አካላት መሆናቸው ወይም አለመሆናቸው ግልፅ ባይሆንም አሠራር እንደሚያሣየው ሀገሮች እንዲህ አይነት ህንፃዎች ወታደራዊ ዒላማ ሆነው ጥቃት ቢፈፀምባቸው ሊከሠት የሚችለውን የከፍተኛ ኪሣራ አደጋ ያውቁታል፡፡ ስለዚህም በማንኛውም የጦር ግጭት ወቅት የአደገኛ ሀይሎች አምልጦ መውጣትና በሲቪሉ ህዝብ ላይ ከፍተኛ ኪሣራ መድረስን ለማስቀረት በጥቃት ወቅት የተለየ ጥንቃቄ እንደሚያስፈልግ ያውቃሉ፡፡ እናም ይህ ተፈላጊ ነጥብ በማንኛውም አይነት የጦር ግጭት ወቅት ተፈፃሚነት ያለው የልማዳዊ አለምአቀፍ ህግ አካል ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በተጨማሪ ኘሮቶኮል I ውስጥ የተካተተ ሌላ አዲስ ደምብ በተፈጥሮአዊ አካባቢ ላይ ስፋት ያለው ፣ ለረጅም ጊዜ የሚቆይና ከባድ ጉዳት እንዲያስከትሉ የታቀዱ ወይም ያስከትላሉ ተብለው የሚታሰቡ ጦርነት የማካሄድ መንገዶችን መጠቀምን የሚከለክል ነው፡፡ ምንም እንኳን አንዳንድ ሀገሮች ይህ ደምብ ኑክሊየር የጦር መሣሪያዎችን በተመለከተ ተፈፃሚነት ስለሌለው ኑክሊየር የጦር መሣሪያዎችን በተመለከተ ደምቡ በእነርሱ ላይ አሣሪነት እንደሌለው በተደጋጋሚ ቢገለፁም ተጨማሪ ኘሮቶኮል I ከፀደቀ ወዲህ ይህ ክልከላ በሀገራዊ አሠራር እጅግ ሰፊ

---

[68] Additional Protocol I, Article 56(1) (followed, however, by exception in paragraph 12) and Additional
Protocol II, Article 15 (with no exceptions)

ድጋፍ በማግኘቱ ወደ ልማዳዊ ህግነት ተቀይሯል፡፡[69] ከዚህ ደምብ ባሻገር በጥናቱ ግኝት መሠረት የተፈጥሮ አካባቢም እንደ ሲቪል ንብረት የሚቆጠር በመሆኑ ለሌሎች ሲቪል ንብረቶች ጥበቃ በሚያደርጉ መርሆች እና ደምቦች በተለይ ለይቶ የመመልከት ፣ የተመጣጣኝነት ና በጥቃት ወቅት ጥንቃቄ የማድረግ መርሆች የተጠበቀ ነው፡፡

ይህ ማለት የትኛውም የተፈጥሮ አካባቢ አካል ወታደራዊ ኢላማ ካልሆነ በስተቀር መጠቃት የለበትም፡፡ ቢሆንም በወታደራዊ ኢላማ ላይ የሚደረግ ጥቃት በአካባቢ ላይ ከሚጠበቀው ተጨባጭና ቀጥተኛ ወታደራዊ ጥቅም ጋር ሲተያይ የበለጠ ጉዳት የሚያደርስ ከሆነ የተከለከለ ነው፡፡ ለምሣሌ ለኑክሊየር የጦር መሣሪያዎች ጉዳይ አለምአቀፍ ፍርድ ቤት በሰጠው የምክር አስተያየት እንዳስቀመጠው፡ "ሀገሮች ህጋዊ ወታደራዊ አላማዎችን ለማሣካት በሚያደርጉት ጥረት የአካባቢን ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት አስፈላጊውና ተመጣጣኝ የሆነው ምንድን ነው የሚለውን መገምገም አለባቸው"[70] በተጨማሪም በግጭት ውስጥ ተሣታፊ የሆኑ ወገኖች በግጭት ወቅት በአካባቢ ላይ ሊደርስ የሚችልን ጉዳት ለማስቀረት እና በተቻለ መጠን ለመቀነስ የተቻላቸውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ይጠይቃሉ፡፡ የተወሠኑ ወታደራዊ ዘመቻዎች በአካባቢ ላይ ስለሚያደርሱት ጉዳት በእርግጠኛነት ለማወቅ የሚያስችል የሣይንሣዊ ዕውቀት አለመኖር በግጭቱ ውስጥ ተሣታፊ የሆነን ወገን ካለበት እንደዚህ አይነት ጥንቃቄ የማድረግ ግዴታ ነፃ አያደርገውም፡፡[71]

በተጨማሪ ፕሮቶኮሎቹ ውስጥ ያልተዳሰሱ ሌሎች ነጥቦችም አሉ፡፡ ለምሣሌ ተጨማሪ ፕሮቶኮሎቹ በሰላም የማስከበር ተልዕኮ የተሰማሩ ሠራተኞችና የንብረቶቻቸው ጥበቃን በተመለከተ የያዙት ምንም ድንጋጌ የለም፡፡ በተግባር ግን

---

[69] See Customary International Humanitarian Law Opicit. (note 4), Vol. I Rule 45.

[70] International Court of Justice, Legality of the Threat or use of Nuclear Weapons, op.cit.(note 8), 30

[71] See Customary International Humanitarian Law,op.cit.(note 4), Vol. I Rule 44

እነዚህ ሠራተኞችና ንብረቶቻቸው ለሲቪሎችና ለንብረቶቻቸው የሚደረገውን አይነት ጥበቃ ተደርጎላቸዋል፡፡ ስለዚህም በተባበሩት መንግስታት ቻርተር መሠረት በሰላም ማስከበር ስራ የተሰማሩ ሠራተኞችና ንብረቶቻቸው በአለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግ መሠረት ለሲቪሎችና ለሲቪል ንብረቶች የሚደረገው ጥበቃ ተጠቃሚ እስከሆኑ ድረስ ጥቃት እንዳይደርስባቸው የሚከለክል ደምብ ወደ ሀገራዊ አሠራርነት አድጎ በአለም አቀፍ ፍርድ ቤት ህግ ውስጥ ተካትቷል፡፡ በአሁኑ ወቅትም በማንኛውም አይነት የጦር ግጭት ውስጥ ተፈፃሚነት ያለው ልማዳዊ ዓለም አቀፍ ህግ አካል ነው፡፡[72]

ግጭቶችን ከማካሄድ ጋር ግንኙነት ያላቸው በርካታ ነጥቦች በሄግ መመሪያዎች ውስጥ ስርዐት ተበጅቶላቸዋል፡፡ እነዚህ መመሪያዎችም ለረጅም ጊዜ አለምአቀፍ በሆኑ የጦር ግጭቶች ውስጥ ልማዳዊ ተደርገው ይቆጠሩ ነበር፡፡[73] አሁን ግን ከደምቦቻቸው መካከል አንዳንዶቹ ዓለምአቀፍ ባልሆኑ የጦር ግጭቶች ውስጥም በልማዳዊነት ተቀባይነት አግኝተዋል፡፡ ለምሣሌ ረጅም ጊዜ ያስቆጠሩት (1) ለወታደራዊ ጥቅም የግድ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር የጠላትን ንብረት ማውደም ወይም መያዝ፡ እና (2) መውረስን የሚከለክሉት ደምቦች ዓለም አቀፍ ባልሆኑ የጦር ግጭቶች ውስጥም እኩል ተፈፃሚነት አላቸው፡፡ መውረስ ማለት የጠላት ወገን የሆነ ሰው የግል ንብረትን በሀይል በመቀማት ለግል ወይም ለራስ ጥቅም ማዋል ማለት ነው፡፡[74] ሁለቱም ክልከላዎች የጠላት ወገን ንብረት የሆኑ ወታደራዊ ቁሳቁስን በጦርነት ማርኮ የመያዝ ልማዳዊ አሠራርን አይፃረሩም፡፡

---

[72] lbid., Rule 33

[73] See. E.g. International Military Tribunal at Nuremberg. Case of the Major War Criminals, Judgment, 1 October 1946,Official Documents, Vol.I,PP.253-254

[74] See Elements of Crimes for the International Criminal Court, Pillage as war crime (Article 8(2)(b)(xci) and
(e)(v)of the Statute of the International Criminal Court).

በልማዳዊ አለምአቀፍ ህግ መሠረት አዛዦች ማንኛውንም አይነት የመገናኛ ዘዴ በመጠቀም ፀበኝነት የሌለበት ግንኙነት መጀመር ይችላሉ፡፡ ነገር ግን እንዲህ አይነት ግንኙነት መደረግ ያለበት በቅን ልቦና ነው፡፡ አሠራር እንደሚጠቁመው ይህ ግንኙነት ፓርላሜንቴይር (Parlementaires) ተብለው በሚታወቁ አገናኞች አማካኝነት ሊከናወን ይችላል፡፡ ፓርላሜንቴር የሚባለው በግጭቱ ተሣታፊ ከሆኑት ወገኖች የአንዱ አባል ሆኖ ከሌላኛው ወገን ጋር ግንኙነት እንዲጀምር ስልጣን የተሰጠውና በዚህም ምክንያት የማይነካ ሠው ነው፡፡ ነጭ ባንዲራ እያውለበለቡ በመንዝ የራስን ፓርላሜንቴርነት ለማሣወቅ የተለመደው ዘዴ አሁንም ጠቃሚ ሆና ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም ተሳታፊ ወገኖች ግንኙነቱን እንዲያመቻችላቸው ሌላ ሶስተኛ ወገንን ሊጠይቁ የሚችሉበት አሠራርም ዕውቅና ያለው ነው፡፡ ሶስተኛ ወገን የሚባለው ለምሣሌ ጠባቂ ሀይል ወይም በምትክነት ሊሠራ የሚችል ገለለተኛና የማያዳላ የዕርዳታ ድርጅት በተለይ ዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ፣ አለም አቀፍ ድርጅት ወይም ሠላም አስከባሪ ሀይል ሊሆን ይችላል፡፡ የተሰበሰበው አሠራር እንደሚያሳየው የተለያዩ ተቋማትና ድርጅቶች በአለም አቀፍም ሆነ ዓለም አቀፍ ባልሆኑ የጦር ግጭቶች ወቅት በተደረጉ ድርድሮች ውስጥ በአገናኝነት እንደሠሩና ይህም አጠቃላይ ተቀባይነት እንዳለው ነው፡፡ የፓርላሜንቴሮችን ስራ የሚመለከቱት ደምቦች ወደኋላ ሄደው የሚነሱት ከሄግ መመሪያዎች ሲሆን ለረጅም ጊዜም በአለም አቀፍ ግጭቶች ወቅት እንደ ልማዳዊ ይቆጠሩ ነበር፡፡ ላለፉት 50 ዓመታት አካባቢ የነበረ አሠራር ላይ በመመርኮዝ ዓለም አቀፍ ባልሆኑ የጦር ግጭቶች ውስጥም ልማዳዊ ሆነዋል፡፡[75]

ባህላዊ ንብረት መጠበቅን በተመለከተ ሁለት የህግ አቅጣጫዎች እንዳሉ አሠራር ያሣያል፡፡ የመጀመሪያው ከሄግ መመሪያዎች የሚጀምር ሲሆን የሚጠይቀውም

[75] See Customary International Humanitarian Law, Op.cit. (note 4). Vol.I, Rules 67-69

በወታደራዊ ዘመቻዎች ወቅት ወታደራዊ ኢላማዎች ካልሆኑ በስተቀር ለሀይማኖት፣ ለስነጥበብ፣ ለሳይንስ፣ ለትምህርት፣ ወይም ለዕርዳታ ስራዎች በሚያገለግሉ ህንፃዎችና ታሪካዊ ቅርሶች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ልዩ ጥንቃቄ እንዲደረግ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በእንደዚህ አይነት ህንፃዎች እና ቅርሶች ላይ የሚደረግ መያዝን ወይም ማውደምን ወይም ሆን ተብሎ የሚደርስ ጉዳትን ይከለክላል፡፡ እነዚህ ደምቦች ለረጅም ጊዜ በአለም አቀፍ የጦር ግጭቶች ውስጥ ልማዳዊ እንደሆኑ ይቆጠሩ የነበረ ቢሆንም አሁን ግን ዓለም አቀፍ ባልሆኑ የጦር ግጭቶች ውስጥም በልማዳዊነት ተቀባይነት አግኝተዋል፡፡

ሁለተኛው አቅጣጫ ደግሞ "ለእያንዳንዱ ህዝብ ባህላዊ ቅርስ ታላቅ ጠቀሜታ ያለውን ንብረት" የሚጠብቀውና እንደዚህ አይነት ንብረትን በቀላሉ ለመለየት የሚያስችል ልዩ ምልክት ያቀረበው የ1954 የሄግ ባህላዊ ንብረትን የመጠበቅ ስምምነት ውስጥ ባሉ ድንጋጌዎች ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ አሁን ያለው ልማዳዊ ህግ የሚጠይቀው ለወታደራዊ ጥቅም የግድ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር እንደዚህ አይነት ንብረቶች ጥቃት እንዳይደርስባቸው እንዲሁም ለጥቃት እና ለውድመት ለሚያጋልጣቸው አገልግሎት እንዳይውሉ ነው፡፡ በተጨማሪም በእንደዚህ አይነት ንብረቶች ላይ የሚፈፀም ማንኛውንም አይነት ስርቆት፣ ዝርፊያ፣ ወይም ለግል ጥቅም ማዋል እንደዚሁም ማንኛውንም አይነት የማበላሸት ድርጊት ይከለክላል፡፡ እነዚህ ክልከላዎች በሄግ ስምምነት ውስጥ ከቀረቡት ድንጋጌዎች ጋር የሚገጣጠሙና በጠቃሚ ባህላዊ ንብረት ጥበቃ ጉዳይ ስምምነቱ በሀገራዊ አሠራር ላይ ያለውን ተፅዕኖ የሚያሣዩ ማስረጃዎች ናቸው፡፡

### የጦር መሣሪያዎች

ከመጠን በላይ ጉዳት ወይም አላስፈላጊ ስቃይ የሚያደርሱ እንደዚሁም በባህሪያቸው ያለምንም ልዩነት ሁሉንም የሚያጠቁ የጦር መሣሪያዎች መጠቀምን የሚከለክሉት አጠቃላይ መርሆች በማንኛውም የጦር ግጭት ውስጥ ልማዳዊ

ሆነው ተገኝተዋል፡፡ በተጨማሪ በአብዛኛውም በእነዚህ መርሆች ላይ በመመርኮዝ ሀገራዊ አሠራር በርካታ ቁጥር ያላቸውን የጦር መሣሪያዎች በመለየት በጥቅም ላይ እንዳይውሉ (ወይም በተወሠነ መንገድ በጥቅም ላይ እንዳይውሉ) በልማዳዊ አለምአቀፍ ህግ መሠረት ክልክሏል፡፡ እነዚህም፡- መርዝ ወይም መርዛማ የጦር መሣሪያዎች፣ ባዮሎጂካዊ የጦር መሣሪያዎች፣ ኬሚካላዊ የጦር መሣሪያዎች፣ አድማ መበተኛዎችን እንደ ጦርነት ዘዴ፣ አረም ማጥፊያዎችን እንደ የጦርነት ዘዴ፣[76] በሰውነት ውስጥ ገብተው በቀላሉ የሚስፋፉ ወይም ጠፍጣፋ የሚሆኑ ጥይቶች፣ በሰውነት ውስጥ ገብተው የሚፈነዱ ጥይቶችን በሰው ላይ መጠቀም፣ ዋናው ጉዳታቸው ቀስ በቀስ የሆነና በሰውነት ውስጥ መኖራቸው በኤክስሬይ ሊታወቅ የማይችል የጦር መሣሪያዎች፣ በአለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግ መሠረት ልዩ ጥበቃ የማግኘት መብት ካላቸው ንብረቶች ወይም ሰዎች ወይም ሲቪሎችን ሊስቡ ከሚችሉ ንብረቶች ጋር በማንኛውም አይነት መንገድ የተገናኙ ወይም የተሳሰሩ የተጠመዱ አሳሳች ፈንጂዎች፣ እንዲሁም ብቸኛው የውጊያ ተግባራቸው ወይም ከውጊያ ተግባራቸው አንዱ ቋሚ አይነስውርነትን ማስከተል ወይም እይታን ማዳከም እንዲሆን ተደርገው በተለይ የተዘጋጁ የጨረር የጦር መሣሪያዎች ናቸው፡፡

በልማዳዊ ህግ ያልተከለከሉ አንዳንድ የጦር መሣሪያዎችም ቢሆኑ እገዳ ሊደረግባቸው ይቻላል፡፡ ለዚህ እንደምሣሌ መሬት ውስጥ የሚቀበሩ ፈንጂዎችንና ተቀጣጣይ የጦር መሣሪያዎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡

---

[76] ይህ ደምብ ሌሎች በርካታ የልማዳዊ አለም አቀፍ ህግ ደምቦችን ይጠቅማል፡ - እነርሱም የባዮሎጂካዊና የኬሚካላዊ የጦር መሣሪያዎች መልከል፣ ወታደራዊ ኢላማ ባልሆነ ተክል ላይ የሚደግ ጥቃት መልከል፣ ከሚጠበቀው ተጨባጭ ወታደራዊ ጥቅም አንፃር ሲታይ ተመጣጣኝ ያልሆነ የሲቪል ህይወት መጥፋት፣ በሲቪል ንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ ወይም ሁለቱንም የሚያስከትል ጥቃት መከልከል፣ እና በተፈጥሮ አካባቢ ላይ ስፋት ያለው፣ ለረጅም ጊዜ የሚቆይ እና ከፍተኛ የሆነ ጉዳት ማድስ መላከል ናቸው፡፡ See ibid., Rule 76

በመሬት ውስጥ የሚቀበሩ ፈንጂዎች ያላቸውን የጅምላ ጉዳት ለመቀነስ እንዲቻል ልዩ ጥንቃቄ መደረግ አለበት፡፡ ይህ ከሚያካትታቸው ውስጥ ለምሣሌ በግጭት ውስጥ ተሳታፊ የሆነና ተቀባሪ ፈንጂዎችን የሚጠቀም ወገን በተቻለ መጠን የተቀበሩባቸውን ቦታዎች መመዝገብ አለበት የሚለው መርህ ይገኝበታል፡፡ በተጨማሪም ግጭቱ ካበቃ በኋላ ተቀባሪ ፈንጂዎችን የተጠቀመ ወገን ፈንጂዎቹን ማስወድ ወይም ሲቪሎች ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ማክሸፍ ወይም የሚወገዱ ቦታን መንገድ ማመቻቸት አለበት፡፡

የኦታዋውን ስምምነት ከ140 በላይ ሀገሮች አፅድቀው ሌሎችም ለማፅደቅ በዝግጅት ላይ በመሆናቸው ብዛት ያላቸው ሀገሮች ፀረ-ሠው ተቀባሪ ፈንጂዎችን መጠቀም፣ ማምረት፣ ማከማቸትና ማስተላለፍን ለማቆም በስምምነት የታሰሩ ናቸው፡፡ ምንም እንኳን ይህ ክልከላ ስምምነቱን ያልፈረሙ ሀገሮች ባላቸው በርካታ ተፃራሪ አሠራር ምክንያት በአሁኑ ወቅት የልማዳዊ አለምአቀፍ ህግ አካል ባይሆንም የኦታዋውን ስምምነት ያላፀደቁና ወዲያው መከልከላቸውን የማይደግፉትን ጨምሮ ሁሉም ሀገሮች ማለት ይቻላል ፀረ-ሠው ተቀባሪ ፈንጂዎች በመጨረሻ እንዲወገዱ ለማድረግ የሚያስችል ስራ መሠራት እንዳለበት ይስማማሉ፡፡

አንድን ሰው የጦር ጉዳተኛ ለማድረግ የሚያስችል ጉዳቱ የቀለለ መሣሪያ መጠቀም የማያዋጣ ካልሆነ በስተቀር ተቀጣጣይ የጦር መሣሪያዎችን በሰው ላይ መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡ በተጨማሪም መሣሪያዎቹ በጥቅም ላይ ከዋሉ በድርጊቱ የሲቪል ህይወት እንዳይጠፋ፣ ሲቪሎች እንዳይጎዱና ሲቪል ንብረቶች ጉዳት እንዳይደርስባቸው የተለየ ጥንቃቄ መደረግ አለበት፡፡

ከእነዚህ ደምቦች አብዛኛዎቹ በመጀመሪያ በአለም አቀፍ የጦር ግጭቶች ውስጥ ብቻ ተፈፃሚነት ከነበራቸው የስምምነት ድንጋጌዎች ጋር የሚገናኙ ናቸው፡፡

በሂደት ያ አካሄድ ተቀይሯል፡፡ ለምሣሌ በ1996 የተወሰኑ የተለመዱ የጦር መሣሪያዎች ስምምነት ኘሮቶኮል II ላይ የተደረገውንና አለም አቀፍ ባልሆኑ የጦር ግጭቶች ውስጥም ተፈፃሚነት ያለውን ማሻሻያ እንዲሁም በቅርቡ በ2001 በተወሰኑ የተለመዱ የጦር መሣሪያዎች ስምምነት ላይ I እስከ IV ድረስ ያሉት ኘሮቶኮሎች ተፈፃሚነታቸው አለም አቀፍ ያልሆኑ የጦር ግጭቶችንም እንዲያካትት ለማድረግ የተደረገውን ማሻሻያ መጥቀስ ይቻላል፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ልማዳዊ ክልከላዎችና እገዳዎች በማንኛውም አይነት የጦር ግጭት ውስጥ ተፈፃሚነት አላቸው፡፡

የዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ በልማዳዊ አለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግ ላይ ጥናት ለማካሄድ ህጋዊ ስልጣን በተቀበለበት ወቅት አለም አቀፍ ፍርድ ቤት በበኩሉ በተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ በጉዳዩ ላይ የምክር አስተያየት እንዲሰጥ በተጠየቀው መሠረት ኑክሊየር የጦር መሣሪያዎችን ለመጠቀም ማስፈራራት ወይም መጠቀም ያለውን ህጋዊነት እየተመለከተ ነበር፡፡ ስለዚህ ዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ የዚህን ጥያቄ ትንተና ብቻውን ላለመስራት ወሰነ፡፡ አለም አቀፍ ፍርድ ቤት በሰጠው የምክር አስተያየት በሙሉ ድምፅ እንዳለው "የኑክሊየር የጦር መሣሪያዎችን ለመጠቀም ማስፈራራት ወይም መጠቀም በጦር ግጭቶች ወቅት ተፈፃሚነት ካላቸው አስፈላጊ ነገሮች በተለይም አለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግ መርሆችና ደምቦች ከሚጠይቋቸው ጋር መጣጣም አለበት፡፡"[77] በርካታ ሀገሮች በተጨማሪ ኘሮቶኮል I ላይ በተደረገው ድርድር የተካፈሉት ኘሮቶኮሉ ኑክሊየር የጦር መሣሪያዎችን መጠቀምን በተመለከተ ተፈፃሚነት አይኖረውም ብለው በማሠብ መሆኑ ሲታሰብ ይህ ግኝት ጠቀሜታ አለው፡፡ የፍርድ ቤቱ አስተያየት የሚለው ግን የግጭቶች አካሄድን የተመለከቱት ደምቦችና የጦር መሣሪያዎች አጠቃቀምን የተመለከቱት አጠቃላይ መርሆች

---

[77] International Court of Justice, legality of the Threat or use of Nuclear Weapons, op.cit. (note 8), p.226.

በኑክሊየር የጦር መሣሪያዎች አጠቃቀም ላይም ተፈፃሚነት አላቸው፡፡ የእነዚህን መርሆችና ደምቦች አጠቃቀምን በተለይ ፍርድ ቤቱ የደረሰበት መደምደሚያ "ኑክሊየር የጦር መሣሪያዎችን ለመጠቀም ማስፈራራት ወይም መሣሪያዎችን መጠቀም በአጠቃላይ በጦር ግጭቶች ውስጥ ተፈፃሚነት ያላቸውን የአለም አቀፍ ህግ ደምቦች በተለይም የሠብአዊነት ህግ ደምቦችን የሚፃረር ይሆናል፡፡"[78] የሚል ነበር፡፡

## መሠረታዊ ዋስትናዎች

መሠረታዊ ዋስትናዎች የሚመለከቱት በግጭቶች ውስጥ ቀጥተኛ ተሳትፎ ማድረጋቸውን ያላቆሙና በግጭቱ ውስጥ ተሳታፊ የሆነ ወገን ሀይል ውስጥ የሚገኙ ሁሉም ሲቪሎችን እንደዚሁም በጦርነት ጉዳት የደረሰባቸውን ሁሉንም ሰዎች ነው፡፡ መሠረታዊ ዋስትናዎች በሁሉም ሰዎች ላይ ተፈፃሚት ያላቸው ስፋት ያላቸው ደምቦች በመሆቸው በጥናቱ ውስጥ የተለያዩ አይነት ሰዎችን በቀጥታ ወደሚመለከቱ ደምቦች አልተከፋፈሉም፡፡

እነዚህ መሠረታዊ ዋስትናዎች በሙሉ አለም አቀፍ እንደዚሁም አለም አቀፍ ባልሆኑ የጦር ግጭቶች ውስጥ ተፈፃሚነት ባለው አለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግ ላይ ጠንካራ መሠረት አላቸው፡፡ በጥናቱ ውስጥ ከመሠረታዊ ዋስትናዎች ጋር ግንኙነት ያላቸው አብዛኛዎቹ ደምቦች የተገለፁት በተለመደው የሠብአዊነት ህግ የቋንቋ አጠቃቀም መሠረት ነው፡፡ ምክንያቱም ይህ ተጓዳኝ ልማዳዊ ደምቡ የያዘውን ሀሣብ እጅግ በተሻለ ስለሚያንፀባርቅ ነው፡፡"[79]

---

78 lbid., See also United Nations General Assembly, 51st session, First Committee, Statement by the International Committee of the Red Cross, UN Doc. AlC. 1/51/PV.8,18 October 1996,p.10,reproduced in International Review of the Red Cross, No. 316,1997,pp.118-119("the lCRC finds, it difficult to envisage how a use of nuclear weapons could be compatible with the rules of International law")

79 እነዚህ ደምቦች የሚካትቷቸው ሲቪሎች እና በጦርነት ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች በሰብአዊነት እና ያለጎጂ አድልዎ መያዝ አለባቸው፣ የሕይወት ማጥፋት መከልከል፣ ስቃይ፣ ጭካኔ የተሞላበት እና ኢሠብአዊ እንደዚሁም ሰብአዊ ክብርን የሚጎዳ አያያዝ በተለይም አዋራጅና

ነገር ግን አንዳንድ ደምቦች የተረቀቁት በርካታ ከአንድ ርዕስ ጋር ግንኙነት ያላቸው ዝርዝር ድንጋጌዎች የያዟቸውን ነጥቦች ለማካተት በሚያስችል መልኩ ሲሆን እነዚህ ድንጋጌዎች በተለይ ክፍያ የሌለው ወይም አግባብ ያልሆነ የግዳጅ ጉልበት ስራ፣ የግዳጅ መሠወሮችና የዘፈቀደ እስሮች የሚከለክል፣ እንዲሁም ቤተሰባዊ ህይወትን ማክበር የሚጠይቀው ደምብን የሚያካትቱ ነበሩ፡፡[80]

አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በአለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ህግ ስር ያለ አሠራር በጥናቱ ውስጥ በተለይ መሠረታዊ ዋስትናዎችን በሚመለከተው ክፍል ተካትቷል፡፡ ይህ የተደረገበት ምክንያት ምንም እንኳን አንዳንድ ድንጋጌዎች በተወሰኑ ሁኔታዎች ውስጥ በአስቸኳይ ጊዜ ወቅት ሳይተገበሩ ቢችሉም በሰብአዊ ህግ ስምምነቶች ውስጥ በግልፅ እንደተቀመጠው አለምአቀፍ የሰብአዊ መብቶች ህግ በጦር ግጭቶች ወቅትም መተግበሩ ስለሚቀጥል ነው፡፡ በጦር ግጭት ወቅት የሰብአዊ መብቶች ህግ መተግበር መቀጠሉ ብዙ ጊዜ በሀገራዊ አሠራር እንደዚሁም በሰብአዊ መብት አካላትና በአለም አቀፍ ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡[81] በቅርቡም ፍርድ ቤቱ በተያዘው የፍልስጥኤም ግዛት ውስጥ ያለውን የመለያ ግድግዳ ግንባታ አስመልክቶ በሰጠው የምክር አስተያየት እንዳረጋገጠው "የሰብአዊ መብት ስምምነቶች የሚያደርጉት ጥበቃ በጦር ግጭት ወቅት አይቆምም" እንደዚሁም ምንም እንኳን በተናጠል አለምአቀፍ የሰብአዊነት ህግን ወይም የሰብአዊ መብቶች ህግን የሚመለከቱ መብቶች ቢኖሩም "የሁለቱንም

ክብርን የሚነካ አያያዝ መከልከል፣ የአካል መቆራረጥ፣ የህክምናና ሳይንሳዊ ሙከራ መልከል፣ አስገድዶ መድፈርና ሌሎች ወሲባዊ ጥቃቶች መልከል፣ ማንኛውም አይነት ባርነትና የባሪያ ንግድ መከልከል፣ የእገታ መከልከል፣ ሰብአዊ ጋሻን መጠቀም መልከል፣ የትክክለኛ የፍርድ ሂደት ዋስትና፣ የጅምላ ቅጣት መከልከል፣ እና በጦርነት ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች እና ሲቪሎች እምነት እና ሀይማኖታዊ ተግባራት ማክበር የሚሉት ናቸው፡፡ See Customary International Humanitarian Law, Supra note 4,Vol.I Rules 87-94,96-97 and 100-104.

[80] lbid., Rules 98-99 and 105.

[81] See Ibid., Introduction to Chapter 32,Fundamental Guaranties

የአለም አቀፍ ህግ ቅርንጫፎች የሚመለከቱ» ሌሎች መብቶች አሉ።[82] ነገር ግን ጥናቱ ልማዳዊ የሰብአዊ መብት ህግን ትንተና የማቅረብ ዓላማ የለውም። በምትኩ በሰብአዊ መብቶች ህግ ስር ያለ አሠራር ተመሣሣይ የአለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግ መርሆችን ለማገዝ፣ ለማጠናከርና ግልፅ ለማድረግ ተካትቷል።

## አተገባበር

የአለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግ አተገባበርን የተመለከቱ በርካታ ደምቦች የልማዳዊ አለምአቀፍ ህግ አካላት ሆነዋል። በተለይ እያንዳንዱ በግጭቱ ተሳታፊ የሆነ ወገን አለምአቀፍ የሰብአዊነት ህግን ማክበርና በጦር ሀይሎቹና ሌሎች በእርሱ ትዕዛዝ ወይም መመሪያና ቁጥጥር ስር ሆነው በሚንቀሣቀሱ ሰዎች ወይም ቡድኖች መከበሩን ማረጋገጥ አለበት። ስለዚህ የታጠቁ ተቃዋሚ ቡድኖችን ጨምሮ በግጭቱ ተሳታፊ የሆነ እያንዳንዱ ወገን ለጦር ሀይሎቹ አለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግን የተመለከተ ትምህርት መስጠት አለበት። ከእነዚህ አጠቃላይ ግዴታዎች ባሻገር በሀገሮች ላይ አሣሪነት ያላቸው ሌሎች የአተገባበር ዘዴዎች በታጠቁ ተቃዋሚ ቡድኖች ላይ ምን ያህል አሣሪነት እንዳላቸው ያን ያህል ግልፅ አይደለም። ለምሣሌ አለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግ መከበሩን ለማረጋገጥ ለጦር ሀይሎች ትዕዛዝና መመሪያ እንዲሰጥ የሚጠይቀው ግዴታ በአለም አቀፍ ህግ ውስጥ የቀረበው ለሀገሮች እንጂ ለታጠቁ ተቃዋሚ ቡድኖች አይደለም። በተመሣሣይም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በትክክለኛው የአለም አቀፍ ሠብአዊነት ህግ አፈፃፀም ደረጃ ላይ የሚገኙ ወታደራዊ አዛዦችን የሚያማክሩ የህግ አማካሪዎችን የማዘጋጀት ግዴታ በሀገሮች ላይ የተጣለ ሲሆን ይህ ግዴታ በታጠቁ ተቃዋሚ ቡድኖች ላይ አልተጣለም።

[82] International Court of Justice, Legal consequences of the Construction of a wall in the Occupied Palestinian Territory, Advisory Opinion, 9 July 2004, & 106

በተጨማሪም አንድ ሀገር ሊመለከተው በሚችል ሁኔታ አለም አቀፍ የሠብአዊነት ህግ ጥሰቶች ሲከሰቱ ተጠያቂ ይሆናል በጥሰቶቹ ለተከሰተው ኪሣራ ወይም ጉዳትም የተሟላ ካሣ እንዲያቀርብ ይጠየቃል፡፡ ታጣቂ ተቃዋሚ ቡድኖች በአባሎቻቸው ለሚፈፀሙ ጥሰቶች በተመሣሣይ ተጠያቂ መሆናቸው እንደዚሁም ተጠያቂ ከመሆኑም ተጠያቂነቱ የሚያስከትለው ምን እንደሆነ ግልፅ አይደለም፡፡ ከላይ እንደተገለፀው ታጣቂ ተቃዋሚ ቡድኖች አለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግን ማክበርና "ሀላፊነትን በሚወስድ ዕዝ" ስር መንቀሣቀስ አለባቸው፡፡[83] ስለዚህ ታጣቂ ተቃዋሚ ቡድኖች ቡድኖቹን የመሠረቱት ሰዎች ለሚፈጽሟቸው ድርጊቶች በሀላፊነት ይጠየቃሉ የሚል መከራከሪያ ማቅረብ ይቻላል፡፡ ነገር ግን ይህ ምን ሊያስከትል ይችላል የሚለው ግልፅ አይደለም፡፡

በተለይም ምንም በበርካታ ሀገሮች ተጎጂዎች በጥፋተኞቹ ላይ የፍትሀብሔር ክስ ሊመሰርቱ የሚችሉ ቢሆንም ታጣቂ ተቃዋሚ ቡድኖች የተሟላ ካሣ ለማቅረብ ምን ያህል ግዴታ እንዳለባቸው ግልፅ አይደለም፡፡

በግለሠብ ደረጃ ያለ ሀላፊነትን በተመለከተ ልማዳዊ አለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግ የጦር ወንጀሎችን በሚፈፅሙ፣ እንዲፈፀሙ ትዕዛዝ በሚሠጡ፣ ወይም ሲፈፀሙ በአዛዥነት ወይም በበላይነት ቦታ በነበሩ ሁሉም ሠዎች ላይ የወንጀል ተጠያቂነት ያስቀምጣል፡፡ የጦር ወንጀሎች ህግ አተገባበር ማለትም የጦር ወንጀሎች ምርመራና በተጠርጣሪዎች ላይ የሚመሠረት ክስ በሀገሮች ላይ ያለ ግዴታ ነው፡፡ ሀገሮች አለም አቀፍ ወይም ድብልቅ ችሎቶችን በማቋቋም ይህን ግዴታቸውን መወጣት ይችላሉ፡፡

---

83 Additional Protocol II, Article 1(1).

## ማጠቃለያ

ጥናቱ እያንዳንዱ የስምምነት ደምብ ያለውን ልማዳዊ ባህሪይ ለመወሰን አልሞከረም፡፡ ነገር ግን ለማድረግ የሞከረው ነጥቦችን በመተንተን ከእነዚህ ነጥቦች ጋር በተገናኘ ያለው ሀገራዊ አሠራር ላይ የተመሠረቱ ምን አይነት የልማዳዊ አለምአቀፍ ህግ ደምቦች መዝዞ ማውጣት ይቻላል የሚለውን ማሣየት ነው፡፡ በጥናቱ ግኝቶች ላይ የሚደረግ አጭር ቅኝት እንደሚያሣየው ግን በስምምነት ህግ ውስጥ የተካተቱት መርሆችና ደምቦች በአሠራር ውስጥ ሠፊ ተቀባይነት ከማግኘታቸው በተጨማሪ በልማዳዊ አለም አቀፍ ህግ ምስረታ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አሣድረዋል፡፡ ከእነዚህ መርሆችና ደምቦች መካከል አብዛኛዎቹ በአሁኑ ወቅት የልማዳዊ አለም አቀፍ ህግ አካላት ናቸው፡፡ ስለሆነም ስምምነቶቹን ቢያፀድቁም ባያፀድቁም በሁሉም ሀገሮች ላይ አሣሪነት ሲኖራቸው አለም አቀፍ ባልሆኑ የጦር ግጭቶች ውስጥ ተሳታፊ በሆኑ ሁሉም ወገኖች ላይ ተፈፃሚነት ያላቸው ደምቦችን በተመለከተም በታጠቁ ተቃዋሚ ቡድኖች ላይም አሣሪነት አላቸው፡፡

ጥናቱ በተጨማሪ የጠቆመው በርካታ የልማዳዊ አለም አቀፍ ህግ ደምቦች በሁለቱም ማለትም በአለም አቀፍ እንዲሁም አለም አቀፍ ባልሆኑ የጦር ግጭቶች ተፈፃሚ እንደሆኑ እንደዚሁም ሀገራዊ አሠራር ምን ያህል ካሉት የስምምነት ህጎች ባሻገር በመሄድ አለም አቀፍ ባልሆኑ የጦር ግጭቶች ውስጥ ተፈፃሚ የሆኑትን ደምቦች እንዳሰፋቸው ነው፡፡ በመሆኑም የግጭቶች አካሄድ መመሪያና በሀገር ውስጥ የጦር ግጭት ወቅት ያለው የሠዎች አያያዝ በስምምነት ህግ ውስጥ ካለው የበለጠ ዝርዝር ያለውና የተሟላ ነው፡፡ ከሠብአዊነትና ከወታደራዊ ዕይታ አኳያ ይህ የበለጠ ዝርዝር ያለውና የተሟላ መመሪያ ምን ያህል በቂ እንደሆነ ህጉ ተጨማሪ ማሻሻያዎች ያስፈልጉት እንደሆነ ለማወቅ ተጨማሪ ምርመራ ያስፈልጋል፡፡

ልክ እንደ ስምምነት ህግ የልማዳዊ አለም አፍ የሰብአዊነት ህግ ደምቦች ውጤታማ አተገባበር ስርጭት፣ ስልጠናና ማስፈፀምን ይጠይቃል፡፡ ቀደም ሲል ባልተደረገባቸው ቦታዎች ሁሉ እነዚህ ደምቦች በወታደራዊ ማኑዋሎችና በብሔራዊ ህጎች ውስጥ ሊካተቱ ይገባል፡፡

ጥናቱ በተጨማሪ ህጉ ግልፅ ያልሆነባቸውን አካባቢዎች ያሣየ ሲሆን ተጨማሪ ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸው ለምሣሌ ፡- አለም አቀፍ ባልሆኑ የጦር ግጭቶች ወቅት ሲቪሎች ለሚለው ፍቺ፣ በግጭቶች ውስጥ ቀጥተኛ ተሣትፎ የሚለው ፅንሠ ሀሣብና የተመጣጣኝነት መርህ የሚያካትተውና አፈፃፀሙ የሚሉትን ነጥቦች ጠቁሟል፡፡

እስከዛሬ ከተገኙት ውጤቶች ገና መሠራት ከሚገባው ስራ አንፃር ጥናቱ መታየት ያለበት እንደ መጨረሻ ሳይሆን የልማዳዊ አለም አቀፍ ህግ መርሆችና ደምቦችን በተመለከተ ግንዛቤን ማሣደግና መግባባትን መፍጠርን ዓላማው ያደረገ እንደ አዲስ ሂደት ጅማሬ ነው፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ጥናቱ ህጉን በመተግበር፣ ግልፅ በማድረግና በማሻሻል ረገድ የዳበረ ውይይት ለማድረግ መሠረት ሊጥል ይችላል፡፡

## ዕዝል፣ የአለም አቀፍ ሰብአዊነት ህግ ልማዳዊ ደምቦች ዝርዝር

*ይህ ዝርዝር የተዘጋጀው በልማዳዊ አለምአቀፍ የሰብአዊነት ህግ ላይ የተደረገው ጥናት ቅፅ I ውስጥ በቀረበው ማጠቃለያ ላይ በመመርኮዝ ነው፡፡ ጥናቱ እያንዳንዱ የአለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ የስምምነት ደምብ ያለውን ልማዳዊነት ባህሪያ ለማወቅ ያለመ ስላልነበረ የግድ ያሉት ስምምነቶች ያላቸውን አወቃቀር አልተከተለም፡፡ "አጦግ" የሚለው ምህፃረ ቃል በአለም አቀፍ የጦር ግጭት ወቀት ተፈፃሚነት ያላቸውን ልማዳዊ ደምቦች የሚያሳይ ሲሆን "ኢያጦግ" የሚለው ደግሞ አለም አቀፍ ያልሆኑ የጦር ግጭቶች ውስጥ ተፈፃሚነት ያላቸውን ልማዳዊ ደምቦች የሚያሳይ ነው፡፡ በኋላኛው ጉዳይ አንዳንድ ደምቦች አሠራር በአጠቃላይ በዚያ አቅጣጫ ቢጠቁምም የስፋቱ መጠን ያነሰ በመሆኑ ምክንያት ተፈፃሚነታቸው "ሊያስኬድ ይችላል" በሚል የቀረቡ ናቸው፡፡*

### ለይቶ የመመልከት መርህ

#### በሲቪሎችና በተዋጊዎች መካከል ያለው ልዩነት

**ደንብ 1፡** በግጭቶች ውስጥ ተካፋይ የሆኑ ወገኖች በሁሉም ጊዜያት ሲቪሎችን ከተዋጊዎች መለየት አለባቸው፡፡ ጥቃቶች መፈፀም ያለባቸው በተዋጊዎች ላይ ብቻ ነው፡፡ በሲቪሎች ለይ ጥቃቶች መፈፀም የለባቸውም፡፡ [አጦግ/ኢያጦግ ]

**ደንብ 2፡** ዋና አላማቸው በሲቪሉ ህዝብ ላይ ሽብርን መፍጠር የሆነ የሀይል ድርጊቶችና ማስፈራራቶች የተከለከሉ ናቸው፡፡ [አጦግ/ኢያጦግ ]

**ደንብ 3፡** ከህክምናና ከሀይማኖት ሠራተኞች በስተቀር በግጭት ውስጥ ተሣታፊ የሆነ ወገን የጦር ሀይል አባላት በሙሉ ተዋጊዎች ናቸው። [አጦግ/አያጦግ ]

**ደንብ 4፡** በግጭት ውስጥ ተሣታፊ የሆነ ወገን የጦር ሀይል የሚያካትተው በዚያ ወገን ውስጥ ለበታቾቹ ድርጊቶች ሀላፊ በሆነ ዕዝ ስር የሚገኙ ሁሉንም የተደራጁ ታጣቂ ሀይሎች፣ ቡድኖችና ዩኒቶችን ነው። [አጦግ]

**ደንብ 5፡** ሲቪሎች የጦር ሀይል አባላት ያልሆኑ ሰዎች ናቸው። ሲቪሉ ህዝብ የሚያካትተው ሲቪሎች የሆኑ ሁሉንም ሰዎች ነው።[አጦግ/አያጦግ ]

**ደንብ 6፡** በግጭቶች ውስጥ በቀጥታ እስካልተሳተፉ ድረስ እንዲሁም በተሳተፉበት ጊዜ ብቻ ካልሆነ በስተቀር ሲቪሎች ከጥቃት የተጠበቁ ናቸው። [አጦግ/አያጦግ]

## በሲቪል ንብረቶችና በወታደራዊ ኢላማዎች መካከል ያለው ልዩነት

**ደንብ 7፡** በግጭት ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ወገኖች በሁሉም ጊዚያት ሲቪል ንብረቶችን ከወታደራዊ ኢላማዎች መለየት አለባቸው። ጥቃቶች መፈፀም ያለባቸው በወታደራዊ ዒላማዎች ላይ ብቻ ነው። በሲቪል ንብረቶች ላይ ጥቃት መፈፀም የለበትም። [አጦግ/አያጦግ ]

**ደንብ 8፡** ንብረቶችን በተመለከተ ወታደራዊ ኢላማዎች በባህርያቸው፣ በሚገኙበት ቦታ፣ በስራቸው ወይም በአጠቃቀማቸው ለወታደራዊ ዕርምጃ ጠቃሚ አስተዋፅኦ በሚያደርጉ እንደዚሁም በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ቢወድሙ፣ በቁጥጥር ስር ቢውሉ ወይም እንዳይሰሩ ቢደረጉ በጊዜው ካለው ሁኔታ አንፃር ግልፅ ወታደራዊ ጥቅም በሚያስገኙ ዒላማዎች ላይ የተወሰኑ ናቸው። [አጦግ/አያጦግ ]

**ደንብ 9፡** ሲቪል ንብረቶች ወታደራዊ ዒላማዎች ያልሆኑ ንብረቶች ሁሉ ናቸው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 10፡** ወታደራዊ ዒላማ ካልሆኑና እስከሆኑበት ጊዜ ድረስ ብቻ ካልሆነ በስተቀር ሲቪል ንብረቶች ከጥቃት የተጠበቁ ናቸው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

### ያለምንም ልዩነት የሚደረጉ ጥቃቶች

**ደንብ 11፡** ያለምንም ልዩነት የሚደረጉ ጥቃቶች የተከለከሉ ናቸው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 12፡** ያለምንም ልዩነት የሚደረጉ ጥቃቶች

ሀ/ በተወሰኑ ወታደራዊ ዒላማዎች ላይ ያላነጣጠሩ፣

ለ/ በተወሰኑ ወታደራዊ ዒላማዎች ላይ በማነጣጠር በጥቅም ላይ ሊውሉ የማይችሉ ውጊያ ዘዴዎችን የሚጠቀሙ፣

ሐ/ የሚያደርሱት ጉዳት አለምአቀፍ የሰብአዊነት ህግ በሚጠይቀው መሰረት ሊገደቡ የማይችሉ የውጊያ ዘዴዎችን የሚጠቀሙጥቃቶች ሲሆኑ

በዚህም ምክንያት በእያንዳንዱ ሁኔታ ውስጥ በወታደራዊ ዒላማዎች እንደዚሁም በሲቪሎችና በሲቪል ንብረቶች ላይ ያለምንም ልዩነት የሚደረጉ ጥቃቶች ናቸው፡፡

**ደንብ 13፡** ተመሳሳይ የሲቪሎችና የሲቪል ንብረቶች ስብስብ ባለበት ከተማ ወይም መንደር ውስጥ የሚገኙ በግልፅ የተራራቁና የተለዩ ወታደራዊ ዒላማዎችን እንደ አንድ ወታደራዊ ዒላማ በመውሰድ የሚደረግ የቦምብ

ድብደባ ወይም በሌላ መንገድ የሚደረጉ ጥቃቶች የተከለሉ ናቸው። [አጠግ/አያጠግ]

## የጥቃት ተጣጣኝነት

**ደንብ 14፡** ከሚያስገኘው ተጨባጭ እና ቀጥተኛ ወታደራዊ ጥቅም አኳያ ሲታይ ተመጣጣኝ ያልሆነ የሲቪል ህይወት መጥፋት፣ የሲቪሎች መቁሰል ፣ የሲቪል ንብረቶች መጎዳት ወይም ከእነዚህ ሁለቱን ወይም ሁሉንም ሊያስከትል የሚችል ጥቃት የተከለከለ ነው። [አጠግ/አያጠግ]

## የጥቃት ወቅት ጥንቃቄዎች

**ደንብ 15፡** በወታደራዊ ዘመቻዎች በሚካሄዱበት ወቅት ሲቪሉ ህዝብ፣ ሲቪሎችና ሲቪል ንብረቶች እንዳይጎዱ ያለማቋረጥ ጥንቃቄ መደረግ አለበት። ሲቪል ህይወት መጥፋት፣ የሲቪሎች መቁሰልና የሲቪል ንብረቶች መጎዳትን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የተቻለው ጥንቃቄ ሁሉ መደረግ አለበት። [አጠግ/አያጠግ]

**ደንብ 16፡** በግጭት ውስጥ ተሣታፊ የሆነ እያንዳንዱ ወገን ጥቃት ያነጣጠረባቸው ወታደራዊ ዒላማዎች መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚቻለውን ሁሉ ማድረግ አለበት። [አጠግ/አያጠግ]

**ደንብ17፡** በግጭት ውስጥ ተሳታፊ የሆነ እያንዳንዱ ወገን ሲቪል ህይወት መጥፋት፣ የጦርነት ማካሄጃ መንገዶችና ዘዴዎችን በሚመርጥበት ወቅት የተቻለውን ጥንቃቄ ማድረግ አለበት። [አጠግ/አያጠግ]

**ደንብ 18፡** በግጭት ውስጥ ተሳታፊ የሆነ እያንዳንዱ ወገን በሚያደርገው ጥቃት ምክንያት ከሚያገኘው ተጨባጭ እና ቀጥተኛ ወታደራዊ ጥቅም አኳያ ሲታይ ተመጣጣኝ ያልሆነ የሲቪል ህይወት መጥፋት፣ የሲቪሎች መቁሠልና የሲቪል ንብረቶች መጎዳት ይከተል እንደሆነ ለመገምገም የተቻለውን ሁሉ ማድረግ አለበት፡፡ [አጦግ/አያጦግ ]

**ደንብ 19፡** በግጭት ውስጥ ተሳታፊ የሆነ እያንዳንዱ ወገን የሚያደርገው ጥቃት ያነጣጠረበት በወታደራዊ ዒላማ እንዳልሆነ ከታወቀ እንደዚሁም ጥቃቱ ሊገኝ ከሚችለው ተጨባጭና ቀጥተኛ ወታደራዊ ጥቅም ጋር ሲተያይ ተመጣጣኝ ያልሆነ የሲቪል ህይወት መጥፋት፣ የሲቪሎች መቁሠልና የሲቪል ንብረቶች መጎዳትን ሊያስከትል የሚችል ከሆነ ጥቃቱን ለመሠረዝ ወይም ለማዘግየት የተቻለውን ሁሉ ማድረግ አለበት፡፡ [አጦግ/አያጦግ ]

**ደንብ 20፡** ሁኔታዎች የማይፈቅዱ ካልሆነ በስተቀር በግጭት ውስጥ ተሳታፊ የሆነ እያንዳንዱ ወገን ሲቪሉን ህዝብ ሊጎዳ የሚችል ጥቃት ከማካሄዱ በፊት በቂ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መስጠት አለበት፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 21፡** ከበርካታ ወታደራዊ ዒላማዎች መካከል የመምረጥ ዕድል ካለ ለጥቃት የሚመረጠው ዒላማ በሲቪሎች ህይወትና በሲቪል ንብረቶች ላይ እጅግ አነስተኛ አደጋ የሚፈጥረው መሆን አለበት፡፡ [አጦግ/አያጦግ (ሊያስኬድ ይችላል)]

## በጥቃት ምክንያት ከሚሠቱ አደጋዎች የሚደረጉ ጥንቃቄዎች

**ደንብ 22፡** በግጭት ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ወገኖች በቁጥጥራቸው ስር የሚገኙ ሲቪል ህዝቦችና ሲቪል ንብረቶችን በጥቃት ምክንያት ከሚከሰቱ

አደጋዎች ለመጠበቅ የተቻላቸውን ጥንቃቄ ሁሉ ማድረግ አለባቸው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 23፡** በተቻለው መጠን እያንዳንዱ በግጭት ውስጥ ተሳታፊ የሆነ ወገን ወታደራዊ ኢላማዎችን ህዝብ በብዛት በሚኖርባቸው አካባቢዎች ውስጥ ወይም አጠገብ ከመመስረት መቆጠብ አለበት፡፡ [አጦግ/አያጦግ (ሊያስኬድ ይችላል)]

**ደንብ 24፡** በተቻለው መጠን እያንዳንዱ በግጭት ውስጥ ተሳታፊ የሆነ ወገን በቁጥጥሩ ስር የሚገኙ ሲቪል ሰዎችንና ንብረቶችን ከወታደራዊ ዒላማዎች ከሚኙበት አካባቢ ማራቅ አለበት፡፡ [አጦግ/አያጦግ (ሊያስኬድ ይችላል)]

## በተለይ የሚጠበቁ ሰዎችና ንብረቶች

***የሕክምናና የሀይማኖት ሰራተኞች እንዲሁም ንብረቶች***

**ደንብ 25፡** ለህክምና ስራ ብቻ የተሰማሩ የህክምና ሰራተኞች በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ መከበርና መጠበቅ አለባቸው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 26፡** አንድን ሰው ከህክምና ስነ ምግባር ጋር የሚጣጣም የህክምና ስራ በመስራቱ መቅጣት ወይም በህክምና ስራ ላይ የተሰማራን ሰው የህክምና ስነምግባርን የሚፃረር ስራ እንዲሰራ ማስገደድ የተከለከለ ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 27፡** ለሀይማኖታዊ ስራ ብቻ የተሠማሩ የሀይማኖት ሠራተኞች በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ መከበርና መጠበቅ አለባቸው፡፡ እነርሱም ከሰብአዊነት ተግባራቸው ውስጥ ጠላትን የሚጎዱ ድርጊቶችን ከፈፀሙ ጥበቃቸውን ያጣሉ፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 28፡** ለህክምና ተግባራት ብቻ የተሰማሩ የህክምና ዩኒቶች በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ መከበርና መጠበቅ አለባቸው፡፡ እነርሱም ከሰብአዊነት ስራቸው ውጭ ጠላትን ለሚጎዱ ድርጊቶች ጥቅም ላይ ከዋሉ ጥበቃቸውን ያጣሉ፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 29፡** ለህክምና ማጓጓዣ ብቻ የተሰማሩ የህክምና ማጓጓዣዎች በሁሉም ሁኔታ ውስጥ መከበርና መጠበቅ አለባቸው፡፡ እነርሱም ከሰብአዊነት ስራቸው ውጭ ጠላትን ለሚጎዱ ድርጊቶች ጥቅም ላይ ከዋሉ ከለላቸውን ያጣሉ፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 30፡** በአለም አቀፍ ህግ መሠረት በጄኔቫ ስምምነቶች የተመለከቱትን አርማዎችን በግልፅ በሚያሣዩ የህክምና እና የሀይማኖት ሠራተኞችና ንብረቶች ላይ ያነጣጠረ ጥቃት የተከለከለ ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

## የሠብአዊነት ዕርዳታ ሰራተኞችና ንብረቶች

**ደንብ 31፡** የሰብአዊ ዕርዳታ ሰራተኞች መከበርና መጠበቅ አለባቸው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 32፡** ለሰብአዊ ዕርዳታ የሚውሉ ንብረቶች መከበርና መጠበቅ አለላበቸው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

## በሰላም አስከባሪ ተልዕኮ የተሰማሩ ሰራተኞችና ንብረቶች

**ደንብ 33፡** በአለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግ መሠረት ለሲቪሎችና ለሲቪል ንብረቶች የሚደረገው ጥበቃ ተጠቃሚ እስከሆኑ ድረስ በተባበሩት መንግስታት ቻርተር መሠረት በሰላም አስከባሪ ተልዕኮ በተሰማሩ ሰራተኞችና ንብረቶች ላይ ያነጣጠረ ጥቃት የተከለከለ ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

## ጋዜጠኞች

**ደንብ 34፡** የጦር ግጭት በሚካሄድበት አካባቢ በሞያዊ ተልዕኮ የተሰማሩ ሲቪል ጋዜጠኞች በግጭቶች ውስጥ በቀጥታ እስካልተሳተፉ ድረስ መከበርና መጠበቅ አለባቸው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

## የሚጠበቁ ቀጠናዎች

**ደንብ 35፡** የቆሰሉ፣ የታመሙና ሲቪል ሰዎችን በግጭቶች ከሚደርሱ ጉዳቶች ለመጠበቅ በተዘጋጀ ቀጠና ላይ ያነጣጠረ ጥቃት የተከለከለ ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ36፡** በግጭት ውስጥ ተሳታፊ የሆኑት ወገኖች በተስማሙበት ከወታደራዊ እንቅስቃሴ ነፃ የሆነ ቀጠና ላይ ያነጣጠረ ጥቃት የተከለከለ ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 37፡** መከላከል በማይደረግለት ሰፈር ላይ የሚደረግ ጥቃት የተከለከለ ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

## ባህላዊ ንብረት

**ደንብ 38፡** በግጭት ውስጥ ተሳታፊ የሆነ እያንዳንዱ ወገን ባህላዊ ንብረትን ማክበር አለበት፡-

ሀ/ ወታደራዊ ዒላማዎች ካልሆኑ በስተቀር ለሀይማኖት፣ ለስነጥበብ፣ ለሣይንስ፣ለትምህርት ወይም ለዕርዳታ ስራ በሚውሉ ህንፃዎች፣ በታሪካዊ ቅርሶች ላይ በወታደራዊ ዘመቻዎች ጉዳት እንዳይደርስ ልዩ ጥንቃቄ መደረግ አለበት፡፡

ለ/ ለወታደራዊ ምክንያት የግድ ካላስፈለገ በስተቀር ለእያንዳንዱ ህዝብ ባህላዊ ውርስ ታላቅ ጠቀሜታ ያለው ንብረት የጥቃት ዒላማ መሆን የለበትም፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 39፡** ለወታደራዊ ምክንያት የግድ ካላስፈለገ በስተቀር ለእያንዳንዱ ህዝብ ባህላዊ ውርስ ታላቅ ጠቀሜታ ያለውን ንብረት ለውድመት ወይም ለጉዳት በሚያጋልጥ መልኩ መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 40፡** በግጭት ውስጥ ተሳታፊ የሆነ እያንዳንዱ ወገን ባህላዊ ንብረትን መጠበቅ አለበት፡፡

ሀ/ ማንኛውም የሀይማኖት፣ የዕርዳታ፣ የትምህርት፣የስነጥበብና ሳይንስ ተቋማት፣ ታሪካዊ ቅርሶችና የስነጥበብና የሳይንስ ስራዎች ላይ የሚደረግ መያዝ፣ ማውደም ወይም ሆን ብሎ ጉዳት ማድረስ የተከለከለ ነው፡፡

ለ/ ለእያንዳንዱ ህዝብ ባህላዊ ቅርስ ታላቅ ጠቀሜታ ባለው ንብረት ላይ የሚደረግ ማንኛውም አይነት ስርቆት፣ ዝርፊያ፣ ወይም ለግል ጥቅም ማዋል ወይም ማንኛውም አይነት ውድመት የተከለከለ ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 41፡** ተቆጣጣሪው ሀይል ከተቆጣጠረው ቦታ የሚደረግን ህገወጥ የባህላዊ ንብረት ወደውጭ መላክን መከላከልና በህገወጥ መንገድ የወጡትንም ንብረቶች በተቆጣጠረው ቦታ ለሚገኙ ባለስልጣናት መመለስ አለበት፡፡ [አጦግ]

### አደገኛ ሀይላትን የያዙ ግንባታዎችና ተቋማት

**ደንብ 42፡** አደገኛ ሀይላት ተለቅቀው በሲቪሉ ህዝብ ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንዳያደርሱ ለመከላከል እንዲቻል እንደ ግድቦች፣ ጎርፍ መከላከያዎች፣ ኑክሊየር ኤሌክትሪክ ሀይል ማመንጫ ጣቢያዎች እና ሌሎች በእነሱ ላይ ወይም አካባቢ ያሉ ተቋማት ላይ ጥቃት ሲሰነዘር ልዩ ጥንቃቄ መደረግ አለበት፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**የተፈጥሮ አካባቢ**

**ደንብ 43፡** ግጭቶችን የማካሄድ አጠቃላይ መርሆች የተፈጥሮ አካባቢን በተመለተም ተፈፃሚነት አላቸው፡፡

ሀ/ ወታደራዊ ዒላማ ካልሆነ በስተቀር የትኛውም የተፈጥሮ አካባቢ አካል መጠቃት የለበትም

ለ/ ለወታደራዊ ጥቅም የግድ ካላስፈለገ በስተቀር የትኛውንም የተፈጥሮ አካባቢ አካል ማውደም የተከለከለ ነው፡፡

ሐ/ ከሚያስገኘው ተጨባጭ እና ቀጥተኛ ወታደራዊ ጥቅም አኳያ ሲታይ ተመጣጣኝ ያልሆነ ጉዳት በአካባቢ ላይ ሊያደርስ የሚችል ጥቃት በወታደራዊ ዒላማ ላይ መክፈት የተከለከለ ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 44፡** ውጊያን የማካሄጃ መንገዶችና ዘዴዎች በጥቅም ላይ ሲውሉ የተፈጥሮ አካባቢ መከላከልና ማቆየትን ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ መሆን አለበት፡፡ በወታደራዊ ዘመቻዎች ወቅት በአካባቢ ላይ ሊደርስ የሚችልን ጉዳት ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ እንዲቻል የተቻለው ጥንቃቄ ሁሉ መደረግ አለበት፡፡ አንድ ወታደራዊ ዘመቻ በአካባቢ ላይ ሊያደርስ

ስለሚችለው ጉዳት የሳይንሳዊ እርግጠኛነት አለመኖር አንድን ወገን እንደዚህ አይነት ጥንቃቄን ከማድረግ ነፃ አያደርገውም። [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 45፡** በተፈጥሮ አካባቢ ላይ ሰፊ፣ ለረጅም ጊዜ የሚቆይና ከባድ ጉዳት የሚያደርስ የውጊያ ማካሄጃ መንገዶችና ዘዴዎችን መጠቀም የተከለከለ ነው። የተፈጥሮ አካባቢን ማውደምን እንደ የጦር መሣሪያ መጠቀም አይቻልም። [አጦግ/አያጦግ (ሊያስኬድ ይችላል።)]

## የተወሰኑ ጦርነት የማካሄጃ ዘዴዎች

### ምህረት መከልከል

**ደንብ 46፡** ምህረት እንደማይኖር ትዕዛዝ መስጠት፣ በዚያ የሚገኝን ጠላት ማስፈራራት፣ ወይም ግጭቶችን በዚህ መልኩ ማካሔድ የተከለከለ ነው። [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 47፡** በጦርነት ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎችን (hors de combat) ማጥቃት የከለከለ ነው። ይህም ማለት፡-

ሀ/ በጠላት ወገን ቁጥጥር ስር የሚገኝ ማንኛውም ሰው

ለ/ ራሱን በመሣቱ፣ በባህር ላይ በደረሰበት አደጋ፣ በመቁሰሉ ወይም በመታመሙ ምክንያት ራሱን መከላከል የማይችል ማንኛውም ሰው ወይም

ሐ/ እጅ ለመስጠት ግልፅ ፍላጎት ያሳየ ማንኛውም ሰው ሲሆን ከማንኛውም የፀብ ድርጊቶች የሚቆጠብና ለማምለጥ የማይሞክር ከሆነ ነው። [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 48፡** በጭንቅ ምክንያት ከአውሮኘላን ላይ በፓራሹት ጃንጥላ በመውረድ ላይ የሚገኙ ሰዎችን የጥቃት ዒላማ ማድረግ የተከለከለ ነው። [አጦግ/አያጦግ]

## የንብረት ማውደምና መያዝ

**ደንብ 49፡** በግጭት ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ወገኖች የጠላት ወገን ንብረት የሆኑ ወታደራዊ ቁሣቁስን በምርኮ መያዝ ይችላሉ፡፡ [አጦግ]

**ደንብ 50፡** ለወታደራዊ ምክንያት የግድ ካላስፈለገ በስተቀር የጠላት ወገን ንብረት ማውደም ወይም መያዝ የተከለከለ ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 51፡** በቁጥጥር ሥር በዋለ ቦታ ውስጥ የንብረቱ መውደም ወይም መያዝ ለወታደራዊ ምክንያት የግድ ካላስፈለገ በስተቀር

ሀ/ ለወታደራዊ ዘመቻ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ተንቀሣቃሽ የመንግስት ንብረት ሊወረስ ይችላል፣

ለ/ የማይንቀሣቀስ የመንግስት ንብረት የሌላን ንብረት በመጠቀም መብት (usufruct) መሠረት መተዳደር አለበት፡፡

ሐ/ የግል ንብረት መከበር አለበት በተጨማሪም መወረስ የለበትም፡፡ [አጦግ]

**ደንብ 52፡** ዝርፊያ የተከለከለ ነው [አጦግ/አያጦግ]

## ርሀብ እና ሰብአዊ ዕርዳታ ማግኘት

**ደንብ 53፡** የሲቪሉን ሕዝብ ማስራብ ጦርነት እንደማካሄጃ ዘዴ መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 54፡** ለሲቪሉ ሕዝብ በህይወት መቆየት የግድ አስፈላጊ የሆነን ንብረት ማጥቃት፣ ማውደም፣ ማስወገድ ወይም ከጥቅም ውጭ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 55፡** በግጭት ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ወገኖች ለተቸገሩ ሲቪሎች የሚቀርብ በባህርይው ገለልተኛ የሆነ እና ያለ ምንም ጎጂ መድልዎ የሚሠጥ የሰብአዊነት ዕርዳታ በፍጥነት እና ያለ እንከን እንዲተላለፍ መፍቀድና ሁኔታውን ማመቻቸት አለባቸው፡፡ መቆጣጠርም ይችላሉ፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 56፡** በግጭት ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ወገኖች ለስራቸው አስፈላጊ የሆኑ የተፈቀደላቸው የሰብአዊነት ዕርዳታ ሰራተኞች በነፃነት መንቀሳቀስ መቻላቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ እንቅስቃሴአቸው በጊዜያዊነት ሊታገድ የሚችለው ለወታደራዊ ጥቅም የግድ አስፈላጊ ሲሆን ብቻ ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

## ማታለል

**ደንብ 57፡** አለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግን እስካልጣሱ ድረስ በጦርነት ውስጥ ማታለሎች የተከለከሉ አይደሉም፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 58፡** የተኩስ ማቆምን የሚያመለክተውን ነጭ ባንዲራ አለአግባብ መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 59፡** በጄኔቫ ስምምነቶች የተመለከቱትን የመለያ ዓርማዎች አለአግባብ መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 60፡** በድርጅቱ ከተፈቀደው ውጪ የተባበሩት መንግስታትን ዓርማና መለዮ መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 61፡** ሌሎች በዓለም አቀፍ ደረጃ የታወቁ ዓርማዎችን መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 62፡** የጠላትን ባንዲራ፣ ወታደራዊ ዓርማ ወይም ምልክት አለአግባብ መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ (ሊያስኬድ ይችላል)]

**ደንብ 63፡** የገለልተኛ ወይም በግጭት ውስጥ ተሳታፊ ያልሆኑ ሌሎች ሀገሮችን ባንዲራ፣ ወታደራዊ ዓርማ ወይም ምልክት መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ (ሊያስኬድ ይችላል)፡፡

**ደንብ 64፡** በስምምነቱ የተማመነን ጠላት በድንገት ለማጥቃት በማሠብ ውጊያን የማቆም ስምምነት ላይ መድረስ የተከለከለ ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 65፡** በሸፈጥ ጠላትን መግደል፣ ማቁሰል ወይም መማረክ የተከከከለ ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

## ከጠላት ጋር የሚደረግ ግንኙነት

**ደንብ 66፡** አዛዦች ማንኛውንም የግንኙነት መንገድ ተጠቅመው ከጠላት ጋር በጠላትነት ላይ ያልተመሰረተ ግንኙነት መጀመር ይችላሉ፡፡ እንዲህ አይነት ግንኙነት መደረግ ያለበት በቅን ልቦና ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 67፡** ፓርላሜንቴሮች አይነኩም፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 68፡** አዛዦች ፓርላሜንተሮች የተሳሳተ የቅድሚያ ግምት እንዳይዙ ለማድረግ አስፈላጊ ጥንቃቄዎችን ማድረግ ይችላሉ፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 69፡** ያላቸውን ቦታ አለምአቀፍ ህግን የሚፃረርና የጠላትን ወገን የሚጎዳ ድርጊት የሚፈፅሙ ፓርላሜንቴሮች ያለመነካት መብታቸውን ያጣሉ፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

## የጦር መሣሪያዎች

### በጦር መሳሪያዎች አጠቃቀም አጠቃላይ መርሆዎች

**ደንብ 70፡** ከመጠን በላይ ወይም አላስፈላጊ ስቃይ የሚያስከትሉ ጦርነት የማካሄጃ መንገዶችና ዘዴዎችን መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 71፡** በባህሪያቸው ያለምንም ልዩነት ሁሉንም የሚያጠቁ የጦር መሣሪያዎችን መጠቀም የከለከለ ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**መርዝ**

**ደንብ 72፡** መርዝን ወይም የተመረዘ የጦር መሣሪያዎችን መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ባዮሎጂካዊ የጦር መሣሪያዎች**

**ደንብ 73፡** ባዮሎጂካዊ የጦር መሣሪያዎችን መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ኬሚካላዊ የጦር መሣሪያዎች**

**ደንብ 74፡** ኬሚካላዊ የጦር መሣሪያዎችን መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 75፡** አድማ መበተኛ ነገሮችን ጦርነት እንደማካሄጃ ዘዴ መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 76፡** አረም ማጥፊያዎችን በሚከተለው ሁኔታ ጦርነት እንደማካሄጃ ዘዴ መጠቀም የተከለከለ ነው፡-

ሀ/ የተከለከሉ የኬሚካል የጦር መሣሪያዎች አይነት ባህሪይ ካላቸው፣

ለ/ የተከለከሉ የባዮሎጂካዊ የጦር መሣሪያዎች አይነት ባህርይ ካላቸው፣

ሐ/ ወታደራዊ ዒላማ ባልሆኑ ተክሎች ላይ ያነጣጠሩ ከሆነ፣

መ/ ከሚያስገኙት ተጨባጭ እና ቀጥተኛ ወታደራዊ ጥቅም አኳያ ሲታይ ተመጣጣኝ ያልሆነ የሲቪል ህይወት መጥፋት፣ የሲቪሎች መቁሠል ወይም የሲቪል ንብረቶች መጎዳትን የሚያስከትሉ ከሆነ፣ ወይም

ሠ/ በተፈጥሮ አካባቢ ላይ ሰፊ፣ ለረጅም ጊዜ የሚቆይና ከባድ የሆነ ጉዳት የሚያስከትሉ ከሆነ [አጦግ/አያጦግ]

**የሚስፋፉ ጥይቶች**

**ደንብ 77፡** በሰውነት ውስጥ ገብተው በቀላሉ የሚሰረጩ ወይም ሰፊ ጉዳት የሚያስከትሉ ጥይቶችን መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**የሚፈነዱ ጥይቶች**

**ደንብ 78፡** በሰውነት ውስጥ ገብተው የሚፈነዱ ፀረ ሰው ጥይቶችን በሰው ላይ መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**በቅድሚያ ተለይተው ሊታወቁ በማይችሉ ፍንጥርጣሪዎች ጉዳት የሚያደርሱ የጦር መሣሪያዎች**

**ደንብ 79፡** ዋነኛ ጉዳታቸው ሰውነት ውስጥ በሚገቡና በኤክስሬይ በማይገኙ ፍንጥርጣሪዎች አማካኝነት የሆኑ የጦር መሣሪያዎችን መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**አሳሳች ወጥመዶች**

**ደንብ 80፡** በማንኛውም አይነት መንገድ በአለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግ መሠረት ልዩ ጥበቃ ከሚደረግባቸው ንብረቶች ወይም ሰዎች ጋር የተነካኩ

ወይም የተያያዙ እንደዚሁም ሲቪሎችን ሊስቡ የሚችሉ አሳሳች ወጥመዶችን መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

### መሬት ውስጥ የሚቀበሩ ፀረ-ሰው ፈንጂዎች

**ደንብ 81፡** መሬት ውስጥ የሚቀሩ ፈንጂዎች በጥቅም ላይ በሚውሉበት ወቅት ያለምንም ልዩነት በጅምላ የሚያደርሱትን ጉዳት ለመቀነስ የተለየ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 82፡** መሬት ውስጥ የሚቀበሩ ፈንጂዎችን የሚጠቀም በግጭት ውስጥ ተሳታፊ የሆነ ወገን በተቻለው መጠን የተቀበሩባቸውን ቦታዎች መመዝገብ አለበት፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 83፡** ግጭቶች በሚያበቁበት ወቅት መሬት ውስጥ የሚቀበሩ ፈንጂዎችን የተጠቀመ በግጭት ውስጥ ተሳታፊ የሆነ ወገን ፈንጂዎቹን ማስወገድ፣ ሲቪሎች ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ማክሸፍ፣ ወይም እንዲወገዱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት አለበት፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

### ተቀጣጣይ የጦር መሣሪያዎች

**ደንብ 84፡** ተቀጣጣይ የጦር መሣሪያዎች በጥቅም ላይ የሚውሉ ከሆነ ያልተጠበቀ የሲቪል ህይወት መጥፋት፣ የሲቪሎች መቁሰል እና የሲቪል ንብረቶች መጎዳትን ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ የተለየ ጥንቃቄ መደረግ አለበት፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 85፡** አንድን ሰው ከአገልግሎት ውጭ የሚያደርግ ጉዳት ለማድረስ ጉዳቱ የቀለለ የጦር መሣሪያ መጠቀም የማይቻል ካልሆነ በስተቀር ተቀጣጣይ የጦር መሣሪያዎችን በሰው ላይ መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

## የሚያሣውሩ የጨረር የጦር መሣሪያዎች

**ደንብ 86፡** ብቸኛው የውጊያ ተግባራቸው ወይም ከውጊያ ተግባራቸው አንዱ ቋሚ አይነስውርነትን ማስከተል ወይም ዕይታን መጋረድ እንዲሆን በተለይ የተዘጋጁ የጨረር የጦር መሣሪያዎችን መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

## የሲቪሎችና ከውጊያ ውጭ የሆኑ ሰዎች አያያዝ

## መሠረታዊ ዋስትናዎች

**ደንብ 87፡** ሲቪሎችና ከውጊያ ውጭ የሆኑ ሰዎች በሰብአዊነት መያዝ አለባቸው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 88፡** በአለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግ ትግበራ ወቅት በዘር፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በሀይማኖት ወይም ዕምነት በፖለቲካ ወይም በሌላ አመለካከት፣ በብሔራዊ ወይም ማህበራዊ ምንጭ፣ በሀብት፣በውልደት ወይም በሌላ ደረጃ፣ ወይም በሌላ በማንኛውም ተመሣሣይ መስፈርት ላይ በመመርኮዝ የሚደረግ ልዩነት የተከለከለ ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 89፡** ህይወት ማጥፋት የተከለከለ ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 90፡** ስቃይ፣ ጭካኔ የተሞላበት ወይም ኢሠብአዊ አያያዝና የግል ክብርን የሚጎዳ በተለይ አዋራጅና ዝቅ የሚያደርግ አያያዝ የተከለከለ ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 91፡** አካላዊ ቅጣት የከለከለ ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 92፡** ግለሰቡ የሚገኝበት የጤንነት ሁኔታ ከሚጠቁመው ውጭ የሆነና በአጠቃላይ ተቀባይነት ካላቸው የህክምና ደረጃዎች ጋር

የማይጣጣም የአካል መቆራረጥ፣ የህክምና ወይም የሳይንሳዊ ሙከራ ማድረግ ወይም ሌላ የህክምና አካሄድን መጠቀም የተከከለ ነው።

**ደንብ 93፡** አስገድዶ መድፈር እንዲሁም ሌሎች የሀይል ወሲባዊ ድርጊቶች የተከለከሉ ናቸው። [አጦግ/አያጦግ]

**ደምብ 94፡** ባርነትና የባሪያ ንግድ በማንኛውም መልኩ የተከለከሉ ናቸው። [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 95፡** ክፍያ የሌለው ወይም አግባብ ያልሆነ የማስገደድ የጉልበት ስራ የተከለከለ ነው። [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 96፡** እገታ የከለከለ ነው። [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 97፡** ሰብአዊ ጋሻዎችን መጠቀም የተከለከለ ነው። [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 98፡** የግዳጅ መሠወር የተከለከለ ነው። [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 99፡** በዘፈቀደ የሚደረግ የነፃነት ክልከላ የተከለከለ ነው። [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 100፡** ማንኛውም ሰው ሁሉንም ህጋዊ ዋስትናዎች ባረጋገጠ ትክክለኛ የፍርድ ሂደት ካልሆነ በስተቀር ወንጀለኛ አይባልም ወይም አይፈረድበትም። [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 101፡** ማንኛውም ሰው አንድ ድርጊት በተፈፀመበት ወይም ባልተፈፀመበት ወቅት በብሔራዊ ወይም በአለም አቀፍ ህግ መሠረት በወንጀልነት በማያስጠይቅ ድርጊት በወንጀል ሊከሰስ ወይም ሊፈረድበት አይችልም። በተጨማሪም የወንጀል ድርጊቱ በተፈፀመበት ወቅት ተፈፃሚነት ከነበረው የከበደ ቅጣትም ሊጣል አይችልም። [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 102፡** በግል የወንጀል ተጠያቂነት ካልሆነ በስተቀር ማንም ሰው በወንጀለኝነት አይጠየቅም። [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ103፡** ጅምላ ቅጣት የተከለከለ ነው። [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 104፡** የሲቪሎችና በጦርነት ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች እምነትና ሀይማኖታዊ አሠራሮች መከበር አለባቸው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 105፡** በተቻለ መጠን ቤተሰባዊ ህይወት መከበር አለበት፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

## ተዋጊዎችና የጦር ምርኮኞነት

**ደንብ106፡** በጥቃት ውስጥ ወይም በወታደራዊ ዘመቻ ዝግጅት ወቅት ተዋጊዎች ራሳቸውን ከሲቪሉ ህዝብ መለየት አለባቸው፡፡ እንደዚህ ካላደረጉ የጦር-ምርኮኛነት ቦታ አይኖራቸውም፡፡ [አጦግ]

**ደንብ 107፡** የስለላ ስራ ሲሰሩ የተያዙ ተዋጊዎች በጦር-ምርኮኛነት የመቆጠር መብት የላቸውም፡፡ ካለቀዳሚ የፍርድ ሂደት ወንጀለኛ ሊባሉ ወይም ሊፈረድባቸው አይቻልም፡፡ [አጦግ]

**ደንብ 108፡** በተጨማሪ ኘሮቶኮል I በተሰጠው ፍቺ መሠረት ቅጥረኛ ወታደሮች የተዋጊነትም ሆነ የጦር- ምርኮኛ ቦታ የማግኘት መብት የላቸውም፡፡ ካለቀዳሚ የፍርድ ሂደት ወንጀለኛ ሊባሉ ወይም ሊፈረድባቸው አይችልም፡፡ [አጦግ]

## የቆሰሉ፣ የታመሙና በባህር ላይ አደጋ የደረሰባቸው

**ደንብ 109፡** ሁኔታዎች በፈቀዱ ጊዜ ሁሉ በተለይ ውጊያ ካበቃ በኋላ በግጭት ውስጥ ተሳታፊ የሆነ እያንዳንዱ ወገን ያለምንም መዘግየት የቆሠሉ፣ የታመሙና በውሀ ላይ አደጋ የደረሰባቸው ሰዎችን የማፈላለግ፣ የማሠባሰብና ከአካባቢው የማስወጣት የሚቻለውን እርምጃ ሁሉ መውሰድ አለበት፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 110፡** የቆሠሉ፣ የታመሙና በባህር ላይ አደጋ የደረሰባቸው ሰዎች ሁኔታቸው የሚጠይቀውን የህክምና እርዳታና ክትትል በሚቻለው የተሟላ ሁኔታና ያለመዘግየት ማግኘት አለባቸው፡፡ በመካከላቸውም በህክምና ካልሆነ በሌላ በምንም ላይ የተመረኮዘ ልዩነት መደረግ የለበትም፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 111፡** በግጭት ተሳታፊ የሆነ እያንዳንዱ ወገን የቆሠሉ፣ የታመሙና በውሀ ላይ አደጋ የደረሰባቸው ሰዎች መጥፎ አያያዝ እንዳይደርስባቸው እንደዚሁም የግል ንብረታቸው እንዳይዘረፍ ለመጠበቅ አስፈላጊ እርምጃዎችን ሁሉ መውሰድ አለበት፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

## የሞቱ ሰዎች

**ደንብ 112፡** ሁኔታዎች በፈቀዱ ጊዜ ሁሉ በተለይ ውጊያ ካበቃ በኋላ በግጭት ውስጥ ተሳታፊ የሆነ እያንዳንዱ ወገን ያለመዘግየት የሞቱ ሰዎችን ያለማዳላት ለማፈላለግ፣ ለማሠባሰብና ከቦታው ለማስወጣት የተቻለውን እርምጃ ሁሉ መውሰድ አለበት፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 113፡** በግጭት ውስጥ ተሳታፊ የሆነ እያንዳንዱ ወገን በተቻለው መጠን የሞቱ ሰዎች እንዳይዘረፉ ለመከላከል አስፈላጊ እርምጃዎችን ሁሉ መውሰድ አለበት፡፡ የሞቱ ሰዎችን አካል መቆራረጥ የተከለከለ ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 114፡** በግጭት ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ወገኖች በተጠየቁ ጊዜ አስከሬኖች ለሚመለከተው ወገን ወይም ለቅርብ ዘመድ እንዲሰጡ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት መጣር አለባቸው፡፡ የግል ንብረቶቻቸውንም መመለስ አለባቸው፡፡ [አጦግ]

**ደንብ 115፡** የሞቱ ሰዎች በክብር መቀበር እንደዚሁም የተቀበሩባቸው ስፍራዎች መከበርና በተገቢ ሁኔታ መጠበቅ አለባቸው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 116፡** የሟቾችን ማንነት ለመለየት እንዲያስችል በግጭት ተሳታፊ የሆነ እያንዳንዱ ወገን ከመቀበራቸው በፊት አስፈላጊ መረጃዎችን መመዝገብና መቃብሮቻቸው ላይ ምልክት ማድረግ አለበት፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

### የጠፉ ሰዎች

**ደንብ 117፡** በግጭት ውስጥ ተሳታፊ የሆነ እያንዳንዱ ወገን በጦር ግጭት ምክንያት መጥፋታቸው ሪፖርት የተደረገ ሰዎች የደረሱበትን ለማወቅ የተቻለውን እርምጃ ሁሉ መውሰድ ሲኖርበት ስላጋጠማቸው ነገር ያለውን ማንኛውንም መረጃ ማካፈል አለበት፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

### ነፃነታቸውን የተነፈጉ ሰዎች

**ደንብ 118፡** ነፃነታቸውን የተነፈጉ ሰዎች በቂ ምግብ፣ ውሀ፣ ልብስ፣ መጠለያና ህክምና ሊቀርብላቸው ይገባል፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 119፡** የአንድ ቤተሰብ አባላት እንደቤተሰብ ሆነው በሚያዙበት ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር ነፃነታቸውን የተነፈጉ ሴቶች ወንዶች ከተያዙበት በተለየ ቦታ መያዝና በሴቶች የቅርብ ቁጥጥር ስር መሆን አለባቸው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 120፡** ቤተሰቦች እንደቤተሰብ ሆነው በሚያዙበት ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር ነፃነታቸውን የተነፈጉ ህፃናት አዋቂዎች ከተያዙበት በተለየ ቦታ መያዝ አለበቸው፡፡

**ደንብ 121፡** ነፃነታቸውን የተነፈጉ ሰዎች ከውጊያ ቀጠና ርቀው በሚገኙና ጤንነታቸውና ንፅህናቸውን በሚጠብቁ ቦታዎች መያዝ አለባቸው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 122፡** ነፃነታቸው የተነፈጉ ሰዎች የግል ንብረቶችን መዝረፍ የተከለከለ ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 123፡** ነፃነታቸውን የተነፈጉ ሰዎች ማንነት ዝርዝር መመዝገብ አለበት፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 124፡**

ሀ/ በአለም አቀፍ የጦር ግጭቶች ወቅት ዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ ነፃነታቸውን የተነፈጉ ሰዎች የታሰሩበትን ሁኔታ ለማረጋገጥና ከቤተሰቦቻቸው ጋር ግንኙነት እንዲመሠርቱ እንዲያደርግ መደበኛ ጉብኝት ሊፈቀድለት ይገባል፡፡ [አጦግ]

ለ/ አለም አቀፍ ባልሆኑ የጦር ግጭቶች ወቅት ዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ አገልግሎቶቹን በግጭቱ ተሳታፊ ለሆኑ ወገኖች በማቅረብና በግጭቱ ምክንያት ነፃነታቸውን የተነፈጉትን ሁሉንም ሰዎች በመጎብኘት የታሰሩበትን ሁኔታ ለማረጋገጥና ከቤተሰቦቻቸው ጋር ግንኙነት እንዲመሠርቱ ማድረግ ይችላል፡፡ [አያጦግ]

**ደንብ 125፡** ነፃነታቸውን የተነፈጉ ሰዎች ከቤተሰቦቻቸው ጋር አግባብነት ባለው ድግግሞሽና የሀላፊዎች ሳንሱር መልዕክት መለዋወጥ ሊፈቀድላቸው ይገባል፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 126፡** አለም አቀፍ ባልሆነ የጦር ግጭት አማካኝነት የታሰሩ ሲቪሎችና ነፃነታቸውን የተነፈጉ ሰዎች እስከሚቻለው ድረስ ጎብኚዎች

በተለይም የቅርብ ዘመዶች እንዲጎበኟቸው ሲፈቅዱላቸው ይገባል። [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 127፡** ነፃነታቸውን የተነፈጉ ሰዎች ያሏቸው ስምምነቶችና ሀይማኖታዊ ተግባራት ሊከበሩላቸው ይገባል። [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 128፡**

ሀ/ የጦር ግጭቶች ካበቁ በኋላ የጦር ምርኮኞች ያለመዘግየት መለቀቅና ወደ ሀገራቸው መመለስ አለባቸው። [አጦግ]

ለ/ ሲቪል እስረኞች መታሰራቸውን አስፈላጊ ያደረገው ምክንያት ሲወገድ በጣም ቢዘገይ ግጭቶቹ እንዳበቁ መለቀቅ አለባቸው። [አጦግ]

ሐ/ አለም አቀፍ ባልሆኑ የጦር ግጭቶች ምክንያት ነፃነታቸውን የተነፈጉ ሰዎች መታሰራቸውን አስፈላጊ ያደረጉት ምክንያቶች ልክ እንደጠፉ መለቀቅ አለባቸው። [አያጦግ]

የተጠቀሱት ሰዎች ያልተጠናቀቀ የወንጀል ጉዳይ ካለባቸው ወይም በህግ የተፈረደባቸውን የእስር ጊዜ ያላጠናቀቁ ከሆነ ነፃነታቸውን እንደተነፈጉ ሊቀጥሉ ይችላሉ።

### መፈናቀልና የተፈናቀሉ ሰዎች

**ደንብ 129፡**

ሀ/ በአለም አቀፍ የጦር ግጭት ተሳታፊ የሆኑ ወገኖች በቁጥጥር ስር በዋለ አካባቢ የሚኖሩ ሲቪል ህዝቦችን ለህዝቦቹ ደህንነት ወይም ወታደራዊ ምክንያቶች ካላስገደዱ በስተቀር በሙሉ ወይም በከፊል ማባረር ወይም በጉልበት ማዘዋወር የለባቸውም። [አያጦግ]

ለ/ አለም አቀፍ ባልሆነ የጦር ግጭት ተሳታፊ የሆኑ ወገኖች በአካባቢ የሚኖሩ ሲቪል ህዝቦችን ለህዝቦቹ ደህንነት ወይም ወታደራዊ ምክንያቶች ካላስገደዱ በስተቀር በሙሉ ወይም በከፊል ማፈናቀል የለባቸውም፡፡ [አያጦግ]

**ደንብ 130፡** ሀገሮች የራሳቸውን ሲቪል ህዝብ ወደተቆጣጠሩት ቦታ ማስገባት ወይም ማዘዋወር አይችሉም፡፡ [አጦግ]

**ደንብ 131፡** መፈናቀል በሚከሠትበት ወቅት የተፈናቀሉት ሲቪሎች መጠለያ፣ ንፅህና፣ ጤንነትን የምግብ ደህንነትን በተመለከተ በአጥጋቢ ሁኔታ ተቀባይ ማግኘታቸውንና የቤተሰብ አባላት አለመለያየታቸውን ለማረጋገጥ ሁሉም አስፈላጊ እርምጃዎች መውሰድ አለባቸው፡፡

**ደንብ 132፡** የተፈናቀሉ ሰዎች ለመፈናቀላቸው ምክንያት የሆኑት ምክንያቶች ሲጠፉ ከራሳቸው ፈቃድ በደህና ወደ ሀገራቸው ወይም ወደመኖሪያ ቦታቸው በደህና የመመለስ መብት አላቸው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 133፡** የተፈናቀሉ ሰዎች የንብረት መብቶች መከበር አለባቸው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

## ጥበቃ እንዲያገኙ የሚፈቀድላቸው ሌሎች ሰዎች

**ደንብ 134፡** በጦር ግጭት ምክንያት የተጎዱ ሴቶች ልዩ የጥበቃ፣ የጤንነትና የድጋፍ ፍላጎቶች መከበር አለባቸው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 135፡** በጦር ግጭት ምክንያት የተጎዱ ህፃናት የተለየ አክብሮትና ጥበቃ የማግኘት መብት አላቸው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 136፡** ህፃናት በጦር ሀይሎች ወይም በታጣቂ ቡድኖች ውስጥ መመልመል የለባቸውም፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 137፡** ህፃናት በግጭቶች ውስጥ እንዲሳተፉ ሊፈቀድላቸው አይገባም፡፡ [አጠግ/አያጠግ]

**ደንብ 138፡** በጦር ግጭቶች ምክንያት የተጎዱ አረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞችና ደካሞች ልዩ ክብርና ጥበቃ የማግኘት መብት አላቸው፡፡ [አጠግ/አያጠግ]

**አተገባበር**

**ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግን ማክበር**

**ደንብ 139፡** በግጭት ውስጥ ተሳታፊ የሆነ እያንዳንዱ ወገን ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግን ማክበርና ህጉ በጦር ሀይሎቹና በትዕዛዙ መሠረት የሚንቀሳቀሱ ወይም በመመሪያው ወይም በቁጥጥሩ ስር ያሉ ሌሎች ሰዎች ወይም ቡድኖች መከበሩን ማረጋገጥ አለበት፡፡ [አጠግ/አያጠግ]

**ደንብ 140፡** ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግን የማክበርና መከበሩን የማረጋገጥ ግዴታ ሌላው ስላደረገው የሚደረግ ወይም ስላላደረገው የሚደረግ አይደለም፡፡ [አጠግ/አያጠግ]

**ደንብ 141፡** እያንዳንዱ ሀገር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በትክክለኛው ቦታ ለሚገኙ ወታደራዊ አዛዦች ዓለምአቀፍ የሰብአዊነት ህግ አተገባበርን በተመለከተ የሚያማክሩ የህግ አማካሪዎችን ማዘጋጀት አለበት፡፡ [አጠግ/አያጠግ]

**ደንብ 142፡** ሀገሮችና በግጭት ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ወገኖች ለጦር ሀይሎቻቸው የአለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግ አፈፃፀምን የተመለከተ ትምህርት መስጠት አለባቸው፡፡ [አጠግ/አያጠግ]

**ደንብ 143፡** ሀገሮች ለሲቪሉ ህዝብ የአለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግ ትምህርት እንዲሰጥ ማበረታታት አለባቸው፡፡ [አጠግ/አያጠግ]

### ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግን ማስፈፀም

**ደንብ 144፡** *ሀገሮች ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግ ላይ በግጭት ውስጥ ተሳታፊ ወገኖች የሚደረጉ ጥሰቶችን ማበረታታት የለባቸውም። በተቻላቸው መጠን በአለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግ ላይ የሚደረጉ ጥሰቶችን ለማስቆም ተፅዕኖ ማድረግ አለባቸው።* [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 145፡** *በአለም አቀፍ ህግ ክልከላ ያልተጣለባቸውን ነገር ግን በተዋጊዎች የሚፈፀሙ የሀይል ድርጊቶች* (belligerent reprisals) *ጥብቅ ሁኔታዎችን* (stringent conditions) *ያስከትላሉ።* [አጦግ]

**ደንብ 146፡** *በጄኔቫ ስምምነቶች ከለላ በተሰጣቸው ሰዎች ላይ የሚፈፀሙ የሀይል ድርጊቶች የተከለከሉ ናቸው።* [አጦግ]

**ደንብ 147፡***በጄኔቫ ስምምነቶችና በሄግ የባህላዊ ንብረቶች ጥበቃ ስምምነት የተጠበቁ ንብረቶች ላይ የሚፈፀሙ የሀይል ድርጊቶች የከለከሉ ናቸው።* [አጦግ]

**ደንብ 148፡** *አለም አቀፍ ያልሆኑ የጦር ግጭቶች ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ወገኖች ወደ ሀይል ድርጊቶች የመዞር መብት የላቸውም። በግጭቶች ውስጥ ቀጥተኛ ተሳትፎ ባላደረጉ ወይም ማድረጋቸውን ባቆሙ ሰዎች ላይ የሚወሰዱ ሌሎች የመልስ እርምጃዎች* (Countermeasures) *የተከለከሉ ናቸው።* [አያጦግ]

### ኃላፊነት እና ካሣ

**ደንብ 149፡** *አንድ ሀገር በሚመለከተው ሁኔታ ለሚፈፀም የአለምአቀፍ የሰብአዊነት ህግ ጥሰቶች ሀላፊነት አለበት። እነዚህም የሚያካትቱት፡-*

*ሀ/ የጦር ሀይሎቹን ጨምሮ በተለያዩ ክፍሎቹ የሚፈፀሙ ጥሰቶችን፣*

ለ/ መንግስታዊ ስልጣንን እንዲጠቀሙ ለፈቀደላቸው ሰዎችና አካላት የሚፈፀሙ ጥሰቶችን፣

ሐ/ በትዕዛዙ መሠረት የሚንቀሣቀሱ ወይም በአመራሩና ቁጥጥሩ ስር ባሉ ሰዎች ወይም ተጣቂ ቡድኖች የሚፈፀሙ ጥሰቶችን፣ እና

መ/ በተራ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች የሚፈፀሙና እንደራሱ ድርጊቶች የሚቆጥራቸው ጥሰቶችን ነው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ150፡** በአለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግ ጥሰት ተጠያቂ የሆነ ሀገር ለደረሰው ኪሣራ ወይም ጉዳት ሙሉ ካሣ እንዲከፈል ይጠየቃል፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**የግለሰብ ኃላፊነት**

**ደንብ 151፡** ሰዎች ለሚፈፅሟቸው የጦር ወንጀሎች በግለሰብ ደረጃ ተጠያቂ ናቸው [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 152፡** አዛዦችና ሌሎች የበላይ ሀላፊዎች እነርሱ በተሰጧቸው ትዕዛዞች ምክንያት ለሚደርሱ የጦር ጉዳቶች ተጠያቂ ናቸው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 153፡** አዛዦችና ሌሎች የበላይ ሀላፊዎች የበታቾቻቸው የጦር ወንጀሎች ሊፈፅሙ ወይም እየፈፀሙ እንደሆነ አውቀው ወይም የማያውቁበት ምክንያት ኖሯቸው ወንጀሎቹ እንዳይፈፀሙ ለማድረግ ወይም ተፈፅመው ከሆነ የሚመለከተውን ሠው ለመቅጣት ያላቸውን ስልጣን ተጠቅመው አስፈላጊና አግባብነት ያለው እርምጃ ካልወሰዱ በጦር ወንጀል ተጠያቂዎች ናቸው፡፡ [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 154፡** *ማንኛውም ተዋጊ በግልፅ ከህግ አግባብ ውጭ የሆነን ትዕዛዝ አልፈፅምም የማለት ግዴታ አለበት፡፡* [አጦግ/አያጦግ] [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 155 ፡** *አንድ የበታች የተሰጠው ትዕዛዝ በግልፅ ከህግ አግባብ ውጭ መሆኑን እያወቀ ወይም የተሰጠው ትዕዛዛ ያለው ከህግ አግባብ ውጭ የሆነ ባህርይን የግድ ማወቅ እያለበት ትዕዛዙን ተቀብሎ ከፈፀመ ከወንጀል ተጠያቂነት አያመልጥም፡፡* [አጦግ/አያጦግ]

## የጦር ወንጀሎች

**ደንብ 156፡** *አለም አቀፍ የሰብአዊነት መብት ላይ የሚፈፀሙ ከባድ ጥሰቶች የጦር ወንጀሎች ናቸው፡፡* [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 157፡** *ሀገሮች የጦር ወንጀሎችን በተመለከተ ዓለምአቀፍ የህግ አስተዳደርን በብሔራዊ ፍርድ ቤቶቻቸው የመተግበር መብት አላቸው፡፡* [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 158፡** *ሀገሮች በዜጎቻቸው ወይም በጦር ሀይሎቻቸው ወይም በድንበራቸው ውስጥ ተፈፅመዋል የሚባሉ የጦር ወንጀሎችን መመርመርና አግባብ ከሆነም ተጠርጣሪዎቹን በህግ መጠየቅ አለባቸው፡፡ በተጨማሪም የህግ አስተዳደራቸው የሚሠራባቸው ሌሎች የጦር ወንጀል አይነቶችን የመመርመርና አግባብ ከሆነም ተጠርጣሪዎቹን በህግ መጠየቅ አለባቸው፡፡* [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 159፡** *ግጭቶች ካበቁ በኋላ በስልጣን ላይ ያሉ ሀላፊዎች በጦር ወንጀሎች ከተጠረጠሩ፣ ከተከሰሱ ወይም ከተፈረደባቸው ሰዎች በስተቀር አለምአቀፍ ባልሆኑ የጦር ግጭቶች ውስጥ ቀጥተኛ ተሳትፎ ላደረጉና በጦር ግጭት ምክንያት ነፃነታቸውን ለተነፈጉ ሰዎች በተቻላቸው መጠን ስፋት ያለው ምህረት ለማድረግ መጣር አለባቸው፡፡* [አያጦግ]

**ደንብ 160፡** የገደብ ህጎች በጦር ወንጀሎች ላይ ተፈፃሚነት የላቸውም። [አጦግ/አያጦግ]

**ደንብ 161፡** ሀገሮች በተቻላቸው መጠን በመተባበር የጦር ወንጀሎች ምርመራ እንዲካሄድና ተጠርጣሪዎች በህግ እንዲጠየቁ ለማድረግ ጥረት ማድረግ አለባቸው። [አጦግ/አያጦግ]

# ዓለም አቀፍ የቀይ መስቀል ግምገማ

መጽሔቱ በዓመት አራት ጊዜ ማለትም በመጋቢት፣ ሰኔ፣ መስከረም እና ታህሳስ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ይታተማል።

በዓመቱ የተመረጡ ጽሁፎች በክፍል ዓለማት ደረጃ በአረብኛ፣ ቻይንኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ራሽያንኛ እና በእስፓኒሽ ቋንቋ ይታተማሉ።

በመጽሔቱ የሚታተሙ ጽሁፎችን ከሚከተለው ድረ-ገጽ በነፃ ማግኘት ይቻላል።
www.icrc. org/eng/review

## ጽሁፎች ማቅረብ

የቀይ መስቀል ዓለምአቀፋዊ የግምገማ መጽሔት ከዓለም አቀፍ የሰብዓዋነት ህግ ፖሊሲና ድርጊት ጋር ግንኙነት ባላቸው ርዕሶች ላይ ጽሁፎችን ለሚያቀርቡ ግብዣውን ያስተላልፋል። ብዙዎቹ ጉዳዮች የሚያተኩሩት በኤዲቶሪያል ቦርድ በሚወሰኑ ልዩ ርዕሶች ላይ ነው። እነዚህ ርዕሶች የወደፊት መልዕክቶች በሚል ርዕስ ከመጽሔቱ ድረ ገጽ ላይ ሊገኙ ይችላሉ። በተለይ ከነዚህ ርዕሶች ጋር ግንኙነት ያላቸው ጽሁፎች ይፈልጋሉ።

ጽሁፎች በአረብኛ፣ ቻይንኛ፣ እንግሊዝኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ራሽያንኛ እና በስፓኒሽ ቋንቋዎች ሊዘጋጁ ይችላሉ። አስፈላጊ ከሆነ የተመረጡት ጽሁፎች ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ ሊተረጎሙ <u>ይችላሉ።</u>

የሚላኩ ጽሁፎች ከዚህ ቀደም ሌላ ቦታ የተላኩ ወይም ተቀባይነት ያገኙ መሆን የለባቸውም። ጽሁፎቹ በአቻ ፀሐፊዎች ክለሳ ይደረግባቸዋል። ለማሳተም የመጨረኛው ውሳኔ የሚሰጠው በዋናው ኤዲተር ነው። ክለሳው ጽሁፎቹን የማስተካከል መብት አለው። ጽሁፎቹ ተቀባይነት ማግኘታቸው ወይም ያለማግኘታቸው ወይም ክለሳ ያስፈልጋቸው እንደሆነ የሚለካው ጽሁፎቹ ከደረሱ በአራት ሳምንታት ጊዜ ውስጥ ነው። ጽሁፎቹ ለደራሲዎቻቸው ተመላሽ አይሆኑም።

ጽሁፎቹ በኢ-ሜይል ለሚከተለው አድራሻ መላክ ይችላሉ። review. gva@icrc.org

### ጽሁፎቹ ማሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

የጽሁፎች ርዝመት ከ5000 እስከ 10,000 ቃላት መሆን አለበት። አጫጭር ጽሁፎች ማስታወሻ ወይም አስተያየት (Notes and comments) በሚለው ክፍል መታተም ይችላሉ።

«የተሳታፊዎች ኢንፎርሜሽን እና የዋቤ መጻህፍት አጠቃቀስ መመሪያ» በሚል ርዕስ ከሚከተለው የመጽሔቱ ድረ ገጽ የበለጠ መረጃ ማግኘት ይቻላል።
www.icrc. org/eng/review

## መጽሔት እንዲላክላቸው ለሚፈልጉ

የሚታተመው መጽሔት ቁጥር ውስን ነው። መጽሔት የሚላክላቸው የተወሰነ ቁጥር ላላቸው የተመረጡ ድርጅቶችና ተቋሞች ነው። ተጨማሪ ማከፋፈል የሚያደረገው የተረፉ መጽሔቶች ካሉ ነው።

መጽሔቱ እንዲላክላቸው የሚፈልጉ ጥያቄአቸውን በሚከተለው አድራሻ መላክ ይችላሉ።

International Committee of the Red Cross (ICRC)
Production, Multimedia and Distribution
19, Avenue de la Paix
CH- 1202 Geneva, Switzerland
f + 41 22 730 27 68
E- mail: shop.gva@ icrc. org
www. icrc. org/eng/shop

© icrc

በመጽሔቱ የታተመ ማንኛውንም ጽሁፍ ገልብጦ መልሶ ለማሳተም ከመጽሔቱ ዋና ኤዲተር ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል። የፈቃድ መጠየቂያ በኤዲቶሪያል ቡድን አድራሻ መላክ ይቻላል።

## ኤዲቶሪያል ቡድን

ዋና ኤዲተር - ቶኒ ፋነር
ኤዲቶሪያል ረዳት - ሮቢን ጌይስ
የህትመት ረዳት - ማሪያን ፔሬዳ

International Review of the Red Cross
19, Avenue de La Paix
CH-1220 Geneva, Switzerland
f + 41 22 734 6001
f + 41 22 733 2057
e-mail: review.gva@ icrc. org

ቅጽ 87 ቁጥር 857 መጋቢት 2005

# ዓለም አቀፍ የቀይ መስቀል ግምገማ



www.icrc.org/eng/review

ICRC